ወደሰ ማይ ዐረገ፤ (ወጣ) በአብ ቀኝ ተቀመጠ፥ ለእርሱ ምስጋና አቅርቡ ማለት ነው። (መዝ 46፥5)

## እዎ በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 24፥44 ጀምሮ እንደምንመለከተው፥

ጌታችን ለደቀ መዛሙርቱ ለሐዋርያት ከእናንተ ጋር ሳለሁ በሙሴ ሕግና በነቢያት፥ እንዲሁም በመዝሙራት ስለ እኔ የተነገረው፣ የተጻፈውም ሊፈጸም ይገበዋል ብዬ እንደነገርኳችሁ ቃሌ ይህ ነው በማለት፥ ስለ እርሱ መከራ መቀበልና ከሙታን ተለይቶ መነሣት፣ በእርሱ ስም ወንጌልን መሰበክ፣ ስለ ንስሐና ስለ ኃጢአት ስርየት አስረዳቸው ባረገ በአሥረኛው ቀንም መንፈስ ቅዱስ ስለሚወርድላቸው እስከዚያ ድረስ በኢየሩሳሌም (በቤተ መቅደሱ) መቆየት እንዳለባቸው ካዘዛቸው በኋላ እያዩት፣ እየባረካቸው ወደ ሰማይ ከፍ ከፍ አለ፤ ዐረገ። (ወጣ) በባሕርይ አባቱ በእግዚአብሔር አብ ቀኝም ተቀመጠ።

## በተጨማሪም እነዚህን ቀስ ብለን እንመልከታቸው፥

<u>1ኛ</u> እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል። (<u>ዮሐ 16፥13</u>)

<u>2ኛ</u> ልባችሁ አይታወክ፣ በእግዚአብሔር እመኑ፣ በእኔ ደግሞ እመኑ፣ በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ። <u>ዮሐ 14፥1 ጀምሮ</u>

<u>3ኛ</u> ደግሞም አርባ ቀን እየታያቸው ስለ እግዚአብሔር መንግሥት እየነገራቸው በብዙ ማስረጃ ከሕማማቱ በኋላ ሕያው ሆኖ ለእነእርሱ ራሱን እያሳያቸው።

ከእነእርሱም ጋር አብሮ ሳለ ከኢየሩሳሌም እንዳይወጡ አዘዛቸው። <u>የሐዋ ሥራ 1፥3</u>

<u>4ኛ</u> መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ። <u>ግብረ ሐዋ (የሐዋ ሥራ) 1፥8</u> እንደዚሁም ሮሜ 10፥1 እና 1ኛ ጴጥ 3፥18 እንመልከት።

<u><<ጥቅሶቹ ከአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ የተወሰዱ ናቸው>></u>





# ምዕራፍ 15።

## በዐለ ጰራቅሊጦስ (ርደተ መንፈስ ቅዱስ) {(መንፈስ ቅዱስ የወረደበት ዕለት)}

ከጌታችን ትንሣኤ ጀምሮ እስከ <u>በዐለ ጰራቅሊጦስ</u> ባለው ጊዜ ውስጥ የሚገኙ ቀናት በቍጥር ኀምሳ እንደመሆናቸው መጠን ወቅቱና ጊዜው በዐለ ኀምሳ በመባል ይታወቃል።

በዐለ ኀምሳ ማለት በቀጥታ ሲተረጐም የኀምሳ ቀናት በዐል ማለት ነው።

ይህ በዐለ ኀምሳ ጌታችን እኛን ለማዳን ሲል የተቀበለውን ልዩ ልዩ ፀዋትወ መከራንና በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ያገኘነውን ፍጹም ሕይወት እያሰብን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እያመሰገን መንፈሳዊ ደስታን የምናደርግበት ወቅት ነው።

በቤተ ክርስቲያናችን ፍትሕ መንፈሳዊ ሕግ መሠረት በበዐለ ኀምሳ ጊዜ በንስሓ ቅጣት የሚሰጥ (የሚታዘዝ) ጾም፣ ቀኖና እና የንስሓ ስግደት የለም።

<u>ይኸውም</u> በዚህ ወቅት ቅጣት፣ ጾም፣ ስግደት፣ ንስሓና የመሳሰለው አለመሰጠቱ፥ <u>እንደዚሁም በበዐለ ኀምሳ የሚገኙ ሮብና ዓርብ፥</u> አለመጾማቸውና በገዳምም ሆነ በገጠር የምትገኝ የቤተ ክርስቲያናችን ቅዳሴ ሁሉ በነግህ (በጧት) መሆኑ በመንግሥተ ሰማያት ጾም፣ ረኀብ፣ ኀዘን፣ መከራና ችግር እንደሌለ ለማመልከት እንደሆነ በሊቃውተ ቤተ ክርስቲያን አባቶቻችን ጉባኤ ይነገራል።

በበዐለ ኀምሳ መጨረሻ በኀምሳኛው ቀኑ ደግሞ <u>መንፈስ ቅዱስ ጰራቅሊጦስ በሐዋርያት</u> ላይ የወረደበትን መንፈሳዊ ታሪክንና ምሥጢሩን የምናስታውስበት ዕለት ነው።

በበነገታው ሰኞም የሐዋርያት ጾም ይገባል ማለት ነው።

## <u>የበዐለ መንፈስ ቅዱስ (የጰራቅሊጦስ) የዕለቱ ምስባክ፥</u>

<u>በግእዙ</u> << ልበ ንጹሐ ፍጥር ሊተ እግዚኦ፥
መንፈሰ ርቱዓ ሐድስ ውስተ ከርሥየ፥
ኢትግድፈኒ እምቅድመ ገጽከ>> ይላል።

አማርኛው በትርጓሜው መሠረት ተብራርቶ ሲገለጽም፥ አቤቱ ንጹሕ ልብን ፍጠርልኝ፥ የቀናውንም መንፈስ በውስጤ አድስ፤ ከፊትህ አትጣለኝ ቅዱስ መንፈስህንም ከእኔ ላይ አትውሰድብኝ፤ የማዳንህን ደስታ ስጠኝ ይላል። (መዝ 50፥10 ከዚህ በላይ በተከታታይ እንደተገለጸው ጌታችን ወደ ሰማይ በሚያርግበት (በሚወጣበት) ጊዜ ለደቀ መዛሙርቱ ለሐዋርያት መንፈስ ቅዱስ እንደሚወርድላቸው በነገራቸው መሠረት፥ በተነሣ በኀምሳኛው ቀኑ፤ ባረገም በአሥረኛው ቀኑ በጽርሐ ጽዮን (በጽዮን አዳራሽ) ተሰብስበው ሳሉ የዓለምን ቋንቋዎች ሁሉ የሚያውቁበት፥ አጽናኝ፤ ኃይልንና ብርታትን የሚሰጥ፤ ምሥጢራትን ሁሉ የሚገልጽ፥ ጰራቅሊጦስ መንፈሰ ጽድቅ፤ የእውነት መንፈስ፥ (መንፈስ ቅዱስ) ወረደላቸው። የሐዋ ሥራ 2፥1 ርኩስ መንፈስ ስለ አለ ከዚያ ሲለየው መንፈሰ ጽድቅ፤ የእውነት መንፈስ፥ (መንፈስ ቅዱስ) ይለዋል ይላሉ ሊቃውንት አባቶቻችን በጉባኤያቸው። ዘሩም <<ነፍሰ, ነፈሰ>> ከሚል የግእዝ ግስ ነፋስ፤ መንፈስ ብሎ ይገኛል። ስለ ሆነም ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው የማስተማር፤ (ቅዱስ ወንጌልን የመስበክ) ድውያንን የመፈወስና ሙታንንም የማንሣት ሥራቸውን በጾምና በጸሎት ጀመሩ።

አዎ በቅዱሳት መጻሕፍት በየክፍሉ ተዘግቦ እንደምናገኘው ቅዱሳን ሐዋርያት ጌታችን በዋለበት እየዋሉ፤ ባደረበትም እያደሩ፥ በሚሔድበት ሁሉ እርሱን ተከትለው እየሔዱ በቀጥታ ከእርሱ የተማሩትን ንጹሑን የቅዱስ ወንጌል ቃል ለመላ ዓለም አስተማሩ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንም ይህን ምንም ያልተቀላቀለበትን የክርስቶስን ንጹሕ ትምህርት ነው ከሐዋርያት አንሥቶ በሃይማኖታዊ ትውፊት (ቅብብሎሽ) ከእውነተኞች አበው ሊቃውንተ ቤተክርስቲያንና ከቅዱሳት መጻሕፍት በተላለፈላት መሠረት አንድን ነገር ሳትቀላቅል ሕዝበ ክርስቲያኗን እያስተማረች የምትገኘው።

በመሆኑም ቅዱስ ጳውሎስ በ2ኛው የጢሞ መልእክቱ በምዕ 3፥14 ጀምሮ አንተ ግን በተማርኸበትና በተረዳኸበት ጸንተህ ኑር በማለት እንደመከረን፥ እኛ የኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ልጆች ትክክለኛውን እምነታችን ከማን እንደተማርነው እናውቃለንና፤ የቱ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት እውነተኛ ትምህርት እንደሆነ በማስተዋል በሚገባ ስለምንረዳ በየጊዜው በሚነፍሰው የኑፋቄ (የጥርጥር) ነፋስ የምንደናገር አይደለንም።





ቅዱስ ጳውሎስ በ2ኛ ተሰሎንቄ መልእክቱ በምዕራፍ 2፥15ም <<ወንድሞች ሆይ ጸንታችሁ ቁሙ በቃላችንም ቢሆን ወይም በመልእክታችን የተማራችሁትን ወግ ያዙ>> በማለት እንደመከረን መሠረታዊ እምነታችንንና መንፈሳዊ ታሪካችንን ጠንቅቀን በማወቅ አሁንም በተማርነው መሠረት መጽናት ይገባናል። በጊዜያዊ የፍልስፍና ዕድገት እየተመሠረተ ሁል ጊዜ የሚነዋወጠው የኑፋቄ (የጥርጥር) ማዕበል እንዳይገለባብጠን፤ የክህደት ባሕሩም እንዳያሰጥመን፥ በእየሸንተረሩ የሚወርደው አዳዲስ የማደናገሪያና የማታለያ ጐርፍም አደባልቆ እንዳይወስደን። ስለ እምነታችንና ስለሃይማኖታዊ ሥርዓታችን አፈጻጸም ከቤተ ክርስቲያናችን እውነተኞች ምሁራን እየጠየቅን፤ በሚገባም እየተረዳን፤ ምንጊዜም ተገቢውን መንፈሳዊ ዝግጅት በማድረግ በቅዱስ መንፈሳዊ ሰይፍ የሚመሰለውን ቃለ እግዚአብሔር ታጥቀን ነቃ ብለን መኖር ያስፈልገናል። ኤፌ 6፥11

በተጨማሪም እነዚህን ጥቅሶች እንመልከታቸው፥

1ኛ አሥራ አንዱ ደቀ መዛሙርቱ ግን ወደ ገሊላ ሔዱ፤ ባዩትም ጊዜ ሰገዱለት የተጠራጠሩም ነበሩ። ኢየሱስም ቀረበና እንዲህ ብሎ ተናገራቸው፥ ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ እንግዲህ ሒዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፤ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው። <<እነሆ እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ>> ማቴ 28፥16 ይህ የአምላካችን ቅዱስ ቃል ለጊዜው የተነገረው ለሐዋርያት ቢሆንም የፍጻሜው ዋና መልእክት ግን ለሐዋርያት ብቻ ሳይሆን እንደ ሐዋርያት መልካሙን ሥራ የሚሠሩ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ የሚነሡትን ሁሉንም የእግዚአብሔር አገልጋዮችን ይመለከታል።

2ኛ <<የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል>> ዮሐ 14፥23።

3ኛ በዐለ ኀምሳም የተባለው ቀን በደረሰ ጊዜ ሁሉም በአንድ ልብ ሆነው አብረው ሳሉ ድንገት እንደሚነጥቅ ዐውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምፅ መጣ። ተቀምጠው የነበሩበትንም ቤት ሁሉ ሞላው እንደ እሳትም የተከፋፈሉ ልሳኖች ታዩዋቸው በእያንዳንዳቸውም ላይ ተቀመጡባቸው። በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው በሌላም ልሳኖች ይናገሩ ጀመር። የሐዋ ሥራ) 2፥1።

<<በዐለ ኀምሳ>> ማለት ከትንሣኤው ጀምሮ እስከ በዐለ

እምነት (ሃይማኖት) በልብ የሚታሰብ ከተስፋ ጋር የተያያዘ የማይታይ ረቂቅ ሲሆን፥ በተግባር ሲገለጽ ግን ውጤትን በማሳየት ጉልቶ የሚታይ፥ ባለቤትና ተሳቢ (አድራጊና ተደራጊ) ያለበት ነው።

የሁሉም ሥራ መሠረቱ እምነት (ሃይማኖት) እንደመሆኑ መጠን የሆነ ይሁን ሥራ በእምነት ላይ ካልተመሠረተ ዋጋ የለውም።

በመሆኑም አንድን ተግባር ለመፈጸም ከታሰበ ከሁሉ በፊት ምንም ጥርጥር የሌለበት ልባዊ እምነት ሊኖር ይገባል፣ ከዚያም እምነቱን በሥራ መግለጽ ያስፈልጋል።

ምክንያቱም ጥርጥር ባለበት እምነት ላይ ተመሥርቶ የሚሠራ ሥራ አጥጋቢውን ውጤት የማያስገኝ ከመሆኑም በተጨማሪ እምነትና ሥራ ከተለያዩ ዋጋ እንደሌላቸው በቅዱሳት መጻሕፍትም ተነግሮናል። <u>ለምሳሌ ያዕቆ ምዕራፍ 2፥14 ጀምሮ እንመልከት</u>

አያሌ ምሁራን ስለ እምነት፣ ስለ ተስፋና ስለ ተፈጥሮ በተለያየ ቋንቋ ብዙ ይላሉ፣ ብዙውን ያነሣሉ፣ ብዙውንም ይጽፋሉ። ነገር ግን አብዛኞዎቹ ከኋላው ዋናውን ቁም ነገር እየረሱ ናቸው። <u>ያውም</u> ፈጽሞ ሊረሳ የማይገባው የእምነት፣ የተስፋና የተፈጥሮ ባለቤት የሆነውን ፈጣሪን ነው።

እም መሪ (አስተዳዳሪ) የሌለበት ሀገር፣ ባለቤት የሌለበት ቤት፥ እንዲሁም ሠሪው (ሠራተኛው) የማይታወቅ ሥራ እንደማይኖር ሁሉ፥ ባለቤት (ፈጣሪ) የሌለበት ፍጥረትና እምነትም ሊኖር ስለማይችል እምነትን፣ ተስፋንና ተፈጥሮን ስናነሣ የእነዚህ ሁሉ ባለቤት የሆነውን እግዚአብሔርን ማንሣት፥ ፍጡር በእውቀት ቢጐለብትና ብዙውንም ቢፈላሰፍ ምንም ሊደርስበት የማይችል አምላካዊ ጥበቡንና ድንቅ ሥራውንም ሁሉ ማስተዋል፣ በተግባርም (በሥራም) ማወቅ ተገቢ ነው። <u>ኢሳ 11፥1, 43፥1።</u>

መጽሐፈ መቃብያን ሣልስንም ምዕራፍ ዘጠኝ ከቍጥር አንድ ጀምሮ ብንመለከት ሁሉም በእግዚአብሔር ቍጥጥር መሆኑን ያስረዳናል። <u>መቃ. ሣልስ 9፥1</u>

ብዙ የዓለም ጠበብት አፈርን ቢቆነጥሩ፣ መሬትንም ቢቆፍሩ፣ ከአድማስ እስከ አድማስ ቢዞሩ፣ በምድር ቢሽከረከሩ፣ ወደ ጠፈር (ወደ ሰማይም) ወጥተው ቢመራመሩ መለኮታዊ የሆነውን የእግዚአብሔር ጥበብ ፈጽመው ማግኘት አልቻሉም፣ ወደፊትም አይችሉም።





እም ብዙዎች አዋቂዎች ነን ባዮች ከዓቅማቸው በላይ የሆነውን አምላካዊ ሥራ ሲመራመሩ ከፊሉቹ ከክሕደት ባሕር ገብተው በማዕበሉ ድራሻቸው ሲጠፋ፣ ከፊሎች ደግሞ ግራ ተጋብተው መንገድ ላይ እንደቆሙ ደርቀው ይቀራሉ።

የታደሉ የእግዚአብሔር ወገኖች ግን የፈጣሪአቸውን ድንቅ ሥራ እያደነቁ ሁሉን ማድረግ የሚቻለው እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ይኖራሉ።

እምነት (ሃይማኖት) ማለት፥ ማድረጊያ፣ የሥራ ማስፈጸሚያ፣ የዕቅዶች ማከናወኛ ልባዊ መሣሪያ ሲሆን፥ እምነት (ሃይማኖት) ሲባል ምን እንደሆነ፣ የሚታመነውም ማን እንደ ሆነ አስቀድሞ ማወቅ ተገቢ ነው።

<u>እምነት (ሃይማኖት) በመንፈሳዊ ሕይወት ሲታይ የማመስገኛና የመጸለያ (የመለመኛ) ዋና መሠረት ማለት ነው።</u>

ምክንያቱም በትክክለኛ እምነት ላይ ቆመን ነው መጸለይና ማመስገን የምንችለው።

የሚታመነውና የሚመሰገነውም፥ የእምነትና የስጦታ ባለቤት የሆነው፥ ሰጥቶ የማያልቅበት፣ ከሰጠ በኋላም እንደሰው የማይፀፀት የባሕርይ አምላክ፣ የፍጥረታት ሁሉ ፈጣሪ፣ ሁሉን የሚያስገኝ፣ ከፍጥረት አስቀድሞ የነበረ፣ አሁንም ያለ፣ ዘለዓለም ህልው የሆነ (ለዘለዓለም የሚኖር) ኅልፈት ወይም ሽረት የሌለበት ዘለዓለማዊ ንጉሥ፥ መጀመሪያውና መጨረሻው በፍጡር ሊታወቅ የማይችል፣ ሙሉ ተስፋ የሚጣልበት የባሕርይ አምላክ እግዚአብሔር ነው።

<u>ዘፍ. 1፥1, መጽ. ኩፋ. 2፥1, ኢሳ. 42፥5,ኢዮ. 12፥7, ዮሐ 1፥1, ራዕ. ዮሐ. 22፥12 እንመልከት።</u>

በመንፈሳውያንና በታሪካውያን ጽሑፎች የተመለከትን እንደሆነ ምንም እንኳን አፈጻጸሙና ሁኔታው ሊለያይ ቢችልም ከጥንት ጀምሮ ያለ እምነት የኖረ ሰው ግን እንዳልነበረ ለሁላችንም ግልጽ ነው።

እምነት በተለይም የእግዚአብሔር ልዩ ወዳጅ ተብሎ በሚታወቀው በአብርሃም ዘንድ በመልካም ሥራ ላይ ጎልቶ ታይቷል፤ ለሌላው እውነተኛ አማኝም ትክክለኛ የእምነት ትምህርት ሆኖአል።

እምነት ማለት ምን እንደሆነ፣ የእምነት ባለቤት ማን እንደሆነም በአብርሃም ተግባራዊ የእምነት እንቅስቃሴ ተገልጿል።

አዎ አብርሃም እምነቱን በመልካም ሥራ በመግለጹ ነው የእግዚአብሔር ልዩ ወዳጅ የተባለው።
ዘፍጥ 12፥7, 18፥1, 22፥1 እንመልከት።

እምነት ምንም እንኳን ሥርዓቱና አፈጻጸሙ ሁሉ በሐዲስ ኪዳን ተለይቶ የተቀመጠ ቢሆንም፥ ዋና መሠረታዊ መነሻው ግን ከብሉይ ኪዳን ስለሆነ የብሉይ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍትንም በሚገባ ልንመለከታቸው ይገባናል።

ምክንያቱም የብሉይ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት ለሐዲስ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት መሠረታቸውና ጥሬ ንባባቸው እንደመሆናቸው መጠን፥ የሐዲስ ኪዳን ምንጭ ከብሉይ ኪዳን ነው የሚገኘው።

የሐዲስ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍትም ለብሉይ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት ትርጓሜያቸውና የተግባር ፍጻሜያቸው ናቸው።

ይህም ማለት በዘመነ ኦሪት፥ በሐዲስ ዘመን ምን እንደሚፈጸም በእግዚአብሔር መልእክተኞች ቅዱሳን ነቢያት በትንቢት መልክ ተነግሮ በብሉያት ቅዱሳት መጻሕፍት ተጽፏል።

በዘመነ ኦሪት በቅዱሳን ነቢያት ተነግሮ በብሉያት ቅዱሳት መጻሕፍት የተዘገበው ደግሞ በሐዲስ ዘመን ተግባራዊ ሆኖአል።

ለምሳሌ፥ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ሲሆን፥ ፍጹም ሰው ሆኖ፣ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ፣ በመስቀል ተሰቅሎ ፍጥረቱን ሁሉ እንደሚያድን አስቀድሞ በቅዱሳን ነቢያት ተነግሮ በብሉያት መጻሕፍት ተዘግቧል። ኢሳ 7፥14, ዳን. 7፥13

በብሉይ ኪዳን የተነገረው ትንቢት ደግሞ በሐዲስ ኪዳን ተከናውኗል። ሁሉም በየደረጃው ተፈጽሟል።

ስለ ልደቱ ማቴ 2፥1, ሉቃ 2፥7፥

ስለ ስቅለቱም ማቴ27፥27, ማር 15፥15,ሉቃ 23፥40, ዮሐ 19፥1 ጀምሮ እንመልከት።





## ክፍል 46፥

## የእምነትና የቃል ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት፥

በርእሱ የተጠቀሰው የእምነት ቃል ኪዳን፣ ተፈጥሮና እምነታዊ ተስፋ በዚሁ በእምነትና በቃለ ኪዳን (በቃል ኪዳን) ቅዱሳት መጻሕፍት፥ ውስጥ ይገኛል።

የአምላክን ሥራ ስለሚናገሩ፥ አምላካውያን፣ የአምላክ ልሳናት (የእግዚአብሔር አምላክ ቃላት) በመባል የሚጠሩ ቅዱሳት መጻሕፍት በመሠረታዊ ምሥጢር ሰምና ወርቅ ናቸው።

(81 የሚባሉ ቅዱሳት መጻሕፍት 36 ብሉያትና 35 ሐዲሳት ጠቅላላ 81 ናቸው)

አዎ ጥንታዊውን መንፈሳዊ ሥርዓታችንና ባህላችንን የሚያስረዳን መጽሐፍ ቅዱስ <<ብሉይ ኪዳንና ሐዲስ ኪዳን>> እያለ የራሱ ስም እንደሚጠቀመን በዘመነ ኦሪትና በሐዲስ ኪዳን ዘመን ከእግዚአብሔር የተሰጠን ልዩ ልዩ ቃለ ኪዳን (ቃል ኪዳን) ማለትም ምን ጊዜም የማይለወጥ የውልና የመሐላ ቃልን የያዘ ቅዱስ መጽሐፍም ነው

## ለምሳሌም ብሉይ ኪዳን፥

1ኛ እግዚአብሔር ሰውንም ሆነ ሌላውን ፍጥረቱን ሁሉ ዳግመኛ በጥፋት ውሃ እንደማያጠፋው ከኖኅና ከልጆቹ፣ ከዘራቸውም ጋር ቃለ ኪዳንን (ቃል ኪዳንን) እንዳቆመ (እንደመሠረተ) በብሉይ ኪዳን ቅዱስ መጽሐፍ እናገኛዋለን።
ዘፍ 9፥8 ጀምሮ እንመለከት

2ኛ እግዚአብሔር ከአብርሃምና ከአብርሃም በኋላ ከሚተኩ ከትውልዱ፣ ከዘሩም ሁሉ ጋር የሕይወትና የምሕረት ቃል ኪዳኑን እንዳደረገም በዚሁ በዘፍ 17፥1 ጀምሮ ብንመለከት መረዳት እንችላለን።

3ኛ እግዚአብሔር ከእነሙሴና ከእነአሮን ከሌሎችም ወዳጆቹ አበው ጋር ቃል ኪዳኑን ያደረገበትን የሚገልጽልንም ይህው የብሉይ ኪዳን ቅዱስ መጽሐፍ ነው።

<u>4ኛ</u> ከወዳጆቹ ጋር የተካሔደው ቃለ ኪዳንም ለዘለዓለም የጸና እንደሆነና ምድርንም በቃል ኪዳኑ እንደሚያስባት የተናገረበት በዚሁ በብሉይ ኪዳን ቅዱስ መጽሐፍ ይገኛል።

ይኸውም እግዚአብሔር አምላካችን ምድሪቱንም አስባታለሁ ማለቱ፥ የቅዱሳን፣ የጻድቃንና የሰማዕታት ዓፅም ያረፈበት ቦታ፣ (የተቀበሩበት መካን) ፍጥረቱንና ዓለሙን በሙሉ በቃል ኪዳኑ መሠረት እንደሚጠብቅና በቸርነቱም እንደሚጎበኘን ነው የሚያስረዳን።

<u>(እዝራ ሱቱ 1፥15.ዘሌዋ 26፥42.መዝ 88፥2.88፥28. ዳን 9፥4 እንመልከት)</u>

አዎ ሃይማኖታዊውንና መንፈሳዊውን ታሪካችን ከመነሻውና ከመሠረቱ ጀምረን ስንገልጽ፣ ብሉይ ኪዳንንም ስንል ይህን ቁም ነገር የያዘውን ጥንታዊውን ቅዱስ መጽሐፍ ማለታችን ነው።

## <u>ሐዲስ ኪዳንስ?</u>

ሐዲስ ኪዳንም የብሉይ ኪዳንን ቃል መሠረት አድርጎ ይቀጥላል።

ይኸውም፥

<u>ሀ</u> የሉቃስን ወንጌል ብንመለከት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ ከዘመዷ ከኤልሳቤጥ ጋር ተገናኝታ የእግዚአብሔርን ቸርነት ባደነቀች ጊዜ፥ <u><<ወተዘከረ ሣህሉ ዘይቤሎሙ ለአበዊነ ለአብርሃም ወለዘርዑ እስከለዓለም>></u>

እግዚአብሔር ለአባቶቻችን ለአብርሃም፣ ለይስሐቅና ለያዕቆብ የተናገረውን ምሕረቱንና ይቅርታውን እስከ ዘለዓለም አሰበ።

(አፀና) በማለት ከእግዚአብሔር የተሰጠው የማይሻር የቅዱሳን፣ የጻድቃንና የሰማዕታት ቃል ኪዳን (ቃለ ኪዳን) ለዘለዓለም ፀንቶ ሲያማልድ እንደሚኖር ያስረዳችበት ቃለ ምስጋና (የምስጋና ቃል) በዚሁ መንፈሳዊ ስንሰለቱን ጠብቆ በመጣው በሐዲስ ኪዳን ቅዱስ መጽሐፍ ነው የሚገኘው። <u>ሉቃ 1፥55 1፥71</u>።





<u>ለ</u> ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ እናንተ የነቢያት ልጆችና እግዚአብሔር ለአብርሃም የምድር ወገኖች ሁሉ በዘርህ ይባረካሉ ብሎ ከአባቶቻችን ጋር ያደረገው የኪዳን ልጆች ናችሁ ያለው ቃልም በዚሁ ተዘግቦአል። <u>ግብ.ሐዋ (የሐዋ ሥራ) 3፥25</u>።

አዎ ሐዲስ ኪዳን ስንልም እነዚህ ለምሳሌ የተጠቀሱትና እነዚህን የመሰሉት ቁም ነገሮች የሚገኙበት፣ መሠረቱ የብሉይ ኪዳን ቅዱስ መጽሐፍ የሆነ ቅዱስ መጽሐፋችን ማለታችን ነው።

ብሉይ ማለት የቆየ (ጥንታዊ) ወይም ደግሞ በቀጥተኛ ትርጉሙ ያረጀ ማለት ሲሆን ኪዳን ማለት ደግሞ መሐላ ማለት ነው።

ይኸውም የቆየ (ጥንታዊ) ማለት ነው እንጂ አርጂቶ የተጣለ ማለት አይደለም።

ቃለ ኪዳን (ቃል ኪዳን) ጠቅለል ባለ መልኩ ሲነገርም <u>የመሐላ ቃል (ቃለ መሐላ) ማለት ሲሆን፣</u> ቅድሳት መጻሕፍትም የቃል ኪዳን መጻሕፍት ናቸው ማለት ነው።

ሐዲስ ኪዳን ስንል ደግሞ በዘመነ ብሉይ የነበረውን መሠረት አድርጎ የሚሔድ፣ ቀደም ብሎ በቅዱሳን ነቢያት የተነገረውንና በብሉይ ኪዳን የተዘገበውን፥ ይሆናል፣ ይደረጋል የሚለውን ሆነ ተደረገ እያለ በጽሑፉ ተርጉሞ የሚገኝ፣ በዘመነ ሐዲስ የተሠራውንም በብዛት የያዘ፣ ከክርስቶስ ልደት ወዲህ የተጻፈ የሐዲስ ኪዳን ቅዱስ መጽሐፍ ማለታችን ነው።

አሪታዊው (ጥንታዊው) የብሉይ ኪዳን ቅዱስ መጽሐፍ በሐዲስ ኪዳን ጊዜም እንዳልተሻረ ራሱ ጌታችን በማቴዎስ ወንጌል ነግሮናል። <u>ማቴ 5፥17</u>

<u>ሆኖም በሐዲስ ኪዳን ዘመን አንዳንድ የተሻሻሉ እንዳሉ ግልጽ ነው።</u>

<u>ለምሳሌ ያህልም፥</u> የብሉይ ኪዳን ቅዱስ መጽሐፍ ነፍስን የገደለ ሞት እንደሚገባው ሲፈርድ፥ ሐዲስ ኪዳን (አዲስ ኪዳን) ግን ነፍስ የገደለን ጨምሮ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የኃጢአትን ተግባር የፈጸመ ሁሉ በንስሓ እንዲመለስ፣ መሥዋዕተ ኦሪት በመሥዋዕተ ሐዲስ እንዲሻሻል፣ ጾም፣ ጸሎት፥ የበዐላት አከባበርና

ሃማኖታዊ ሥርዓቱ፥ አገልግሎቱም ሁሉ በሃማኖታዊና በመንፈሳዊ ቀኖና ቤተ ክርስቲያን መሠረት እንዲመራ በሐዲስ ኪዳን ዘመን በጽሑፍ ተጽፎ፤ በክፍልም ተለይቶ ስለታወቀ በመመሪያው መሠረት እየተከናወነ ይገኛል።

ብሉይ ኪዳን ከክርስቶስ ልደት በፊት የነበረው ዘመን አሪት ሲሆን፥ ሐዲስ ኪዳን ግን ከክርስቶስ ልደት ወዲህ ያለው ዘመን ሐዲስ (አዲስ ዘመን) ማለት ነው።

የአባቶቻችን ትርጓሜ ደግሞ ብሉይ ኪዳን አሪት (ምድረ ርስት) ሐዲስ ኪዳን ወንጌል (መንግሥተ ሰማያት) ይላል።

**<<የእሑድ ውዳሴ ማርያም ትርጓሜ>>**

ይህ እንዲጠቀስ ያስፈለገበት ምክንያት የሚነገር ያለው ምሥጢር እነዚህን ቅዱሳት መጻሕፍት መሠረት ያደረገ ስለሆነ ከዚህ በላይ እንደተገለጸው የሁለቱ፥ ማለትም የብሉይ ኪዳንና የሐዲስ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት እንዴት ብለው ተስማምተው እንደሚሔዱ ለማስገንዘብ ያህል ነው።

በመሆኑም ነው ከላይ የብሉይ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት ለሐዲስ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት መሠረታቸውና ጥሬ ንባባቸው እንደመሆናቸው መጠን፥ የሐዲስ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍትም ለብሉይ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት ትርጓሜያቸውና የተግባር ፍጻሜያቸው ናቸው ያልን።

ስለዚህ የብሉዩን (የአሪቱን) መንፈሳዊ ምንጭ መነሻ በማድረግ፥ መንፈሳዊ ታሪኩንና ሃይማኖታዊ ሥርዓቱን ጠብቆ የተላለፈልን አሁን የተተነተነው ቅዱስ መጽሐፋችን እንደሚያስረዳን ከሌሎች ፍጥረታት ሁሉ ለየት ባለ መልኩ በአርአያ እግዚአብሔር ተፈጥሮ በፈጣሪው በእግዚአብሔር ዘንድ ከሌላው ፍጥረት የላቀ ክብርና መብት የተሰጠው ሰው፥ ከሁሉም በፊት ከፈጣሪው፤ ከአምላኩ ከእግዚአብሔር ጋር የሚገናኝበት፤ ፈጣሪው እግዚአብሔርን የሚያገለግልበት፤ የሚያመሰግንበትና የሚያስደስትበት በተስፋ መንግሥተ ሰማያት የተሞላ ምንም ጥርጥር የሌለበት ትክክለኛ እምነት ሲኖረው ይገባል ማለት ነው።

ምክንያቱም ያለ እምነት እግዚአብሔርን ማገልገልም ሆነ ማስደሰት እንደማይቻል በብዙ ክፍል የተገለጸ ሲሆን፥ በጽኑዕ እምነት በመጓዝ ግን ሕይወታዊውን ጥቅም መጨበጥ እንደሚቻል ተረጋግጧል።





ለምሳሌም ዕብራውያን 10፥38 እና 11፥1 ጀምሮ ብንመለከት ስለ እምነትና መሠረታዊ ጥቅሙ በሰፊው መረዳት እንችላለን።

በዐጭሩ ብንጠቅስም፥

1ኛ አብርሃም እግዚአብሔርን እንዳመነና ጽድቅም ሆኖ እንደተቈጠረለት፥ ሮሜ 4፥3

2ኛ ጻድቅ ሰው በእግዚአብሔር <<እምነት>> እንደሚኖር፥ ዕብ 10፥38፤

3ኛ <<እምነት>> ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያረጋግጥልንና የማናየውን የሚያስረዳን እንደሆነ፥ ዕብ 11፥1፤

4ኛ አቤል መሥዋዕቱን <<በእምነት>> ለእግዚአብሔር ባቀረበ ጊዜ እግዚአብሔር እንደ ተቀበለለትና ጻድቅ መሆኑም እንደተመሠከረለት፥ ዘፍ 4፥3 ዕብ 11፥4፤

5ኛ ሄኖክ እንዳይሞት <<በእምነት>> ፈጣሪውን እንደለመነና እግዚአብሔርም ጸሎቱን ተቀብሉ ከሞት እንደሰወረው፥ ዕብ 11፥5፤

6ኛ ያለ እግዚአብሔር <<እምነት>> እግዚአብሔርን ማገልገልም ሆነ ማስደሰት እንደማይቻል፥ ዕብ 11፥6፤

7ኛ የሚጸልይም ሆነ የሚያገለግል ሁሉ አስቀድሞ የእግዚአብሔር ህልውናንና ሰጭነቱንም ከልቡ ማመን እንዳለበት፥ ዕብ 11፥7፤

8ኛ ኖኅ ከፈጣሪው በተነገረው መሠረት መርከቡን በእግዚአብሔር <<እምነት>> እንዳዘጋጀና ከጥፋት ውሃ በመዳንም ጻድቅና የዓለም ወራሽ እንደሆነ፥ ዕብ 11፥7

9ኛ አብርሃም በእግዚአብሔር <<እምነት>> ፈጣሪው ወዳዘዘው ወደ ከነዓን እንደሔደና በከነዓንም ሀገር <<በእምነት>> እንደተጠቀመ ዘፍ 12፥1,17፥8, ዕብራ 11፥8

10ኛ የአብርሃም ሚስት ሣራ ዕድሜዋ ካለፈ በኋላ በእግዚአብሔር <<እምነት>> ደጉን ልጅ ይስሐቅን እንደወለደች÷ ዘፍ 21÷1, ዕብራ 11÷11፣

11 አብርሃም በጽኑዕ <<እምነት>> ልጁ ይስሐቅን ለመሥዋዕት እንዳቀረበና እግዚአብሔርም እንደተቀበለለት+ ዘፍ 22÷9, ዕብራ 11÷17፣

12 ሕዝበ እስራኤል ልክ በደረቅ ምድር እንደሚያልፉ የኤርትራን ባሕር በእግዚአብሔር <<እምነት>> እንደተሻገሩና ጠላቶቻቸው ግን ለመሻገር ሲሞክሩ ባሕሩ ውስጥ እንደሰጠሙ (እንደተዋጡ) ዘፀ 14÷26, ዕብ 11÷29÷

13 ኢያሱና ተከታዮቹ ሁሉ እግዚአብሔርን በማመን በውሃ የተመላውን የዮርዳኖስን ወንዝ እንደተሻገሩና የኢያርኮ ግንብም ሰባት ቀን ከዞሩባት በኋላ በእግዚአብሔር <<እምነት>> እንደወደቀች÷ እንዲሁም ዘማ የምትባለው ረዓብ የኢያሪኮን ሁኔታ እንዲያጠኑ በነዌ ልጅ ኢያሱ ተልከው በእግዚአብሔር <<እምነት>> የመጡትን መልእክተኞች (ሰላዮች) በሰላምና በእግዚአብሔር <<እምነት>> ተቀብላ ከሞት በማትረፏ ከትዕቢተኞች ጋር እንዳልጠፋች÷ ኢያሱ 2÷1, 3÷5, 6÷20, 6÷25, ዕብ 11+30

14 እንደዚሁም እነጌዴዎን፣ እነባርቅ፣ እነሶምሶን፣ እነዮፍታሔ፣ እነዳዊት፣ ሕዝበ እስራኤልና ሌሎችም ነቢያት በእግዚአብሔር <<እምነት>> መንግሥታትን ድል እንደነሡ፣ ጽድቅን እንዳደረጉ፣ ከእግዚአብሔር የተሰጠውን የሕይወትና የተስፋ ቃል እንዳገኙ፣ የአንበሶችን አፍ እንደዘጉ፣ የእሳትን ኃይል እንዳጠፉ፣ ከሰይፍ ስለት እንዳመለጡ፣ ከድካማቸው እንደበረቱ፣ በጦርነት ኃይለኞችን እንደሆኑ፣ የባዕዳንን ጭፍሮች እንዳባረሩ። ዕብ. 11+32

በአጠቃላይ ይህ የተጠቀሰውን ከመጀመሪያው ጀምሮ እስከ ፍጻሜው ድረስ ብንመለከተው የእምነትን መሠረታዊ ጥቅም በሚገባ ያስረዳናል። ዕብ. 10 እና 11÷ ከቍጥር 1 ጀምሮ እንመልከት። ስለ <<እምነት>> ብዙ መጥቀስ የሚቻል ቢሆንም ለምሳሌ ያህል ግን ይህ በቂ ይመስለኛል።





# ክፍል 47÷

## እምነትና መልካም ምግባር÷

የእምነት ትርጉምና አጥጋቢ ውጤት መልካም ሥራ ነው።

ለዚህም ከዚህ ቀጥለው ያሉትን ምሳሌዎች እንመልከት÷

1ኛ ሰው <<በእምነት>> ብቻ ሳይሆን በሥራ እንዲጸድቅ ታያላችሁ እንደዚሁም ጋለሞታይቱ ረዓብ ደግሞ መልእክተኞቹን ተቀብላ በሌላ መንገድ በሰደደቻቸው ጊዜ በሥራ አልጸደቀችምን? ይላል። ያዕ 2÷24, 2÷14, ኢያሱ 2÷1, 6÷25,እንመልከት።

2ኛ መልካም ፍሬ የማያደርግ (የማያፈራ) ዛፍ ይቆረጣል ወደ እሳትም ይጣላል። ማቴ 7÷19 ይህ ቃል ጌታችን የተናገረው ሲሆን ሃይማኖቱን በመልካም ፍሬ በሚመሰለው በመልካም ምግባር የማይገልጽ ሰው ዋጋ እንደሌለው ነው የሚያስረዳን።

3ኛ ነፍስ የተለየው ሥጋ የሞተ እንደሆነ እንዲሁ ደግሞ ከሥራ የተለየ <<እምነት>> የሞተ ነው። ያዕ. 2÷25+

4ኛ እግዚአብሔር አንድ እንደሆነ አንተ ታምናለህ፣ አጋንንትም ያምናሉ ይንቀጠቀጡማል÷ አንተ ከንቱ ሰው <<እምነት>> ከሥራ ተለይቶ የሞተ መሆኑን ልታውቅ ትወዳለህን? ይላል። ያዕ. 2÷19÷

5ኛ አብርሃም ልጁ ይስሐቅን ለመሥዋዕት ማቅረቡ <<እምነቱን>> በሥራ ገልንጿል። ያዕ. 2÷21

6ኛ ሰው <<በእምነት>> ብቻ ሳይሆን በሥራ እንደሚጸድቅ ታያላችሁ ይላል። ያዕ. 2÷24÷

በመሆኑም እምነት በሥራ፣ ሥራም በእምነት ይገለጻል ማለት ነው

ስለዚህ በመንፈሳዊ ሕይወት በኩል እምነት ስንል÷

እግዚአብሔር የባሕርይ አምላክ፣ ፈጣሪ፣ ሁሉን ማድረግ የሚችል መሆኑን፣ ያለእርሱ ምንም ምን ማድረግ የማይቻል፥ በእርሱ ግን የሚሳን ነገር እንደሌለ በሚገባ ማመን፥ በእምነቱ መጽናት፣ በሕጉ መመራት፣ ትእዛዛቱንም መፈጸም፣ እምነትን (ሃይማኖትን) በመልካም ሥራ መግለጽ ማለታችን ነው።

ምክንያቱም እግዚአብሔርን የማይወዱ ሰዎች ሕጉን እንደማይጠብቁና ልቡናቸውም የቀና እንዳይደለ በመጽሐፈ <u>መቃብያን ሣልስ 6፥14</u> የተገለጸ ሲሆን፥ በሕይወት (በጽድቅ) ሊኖርና የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊወርስ የሚፈልግ ሁሉ ትእዛዘ እግዚአብሔርን በመጠበቅ <<በእምነቱ>> ጸንቶ በእግዚአብሔር መንገድ መሔድ እንዳለበትም ከዚህ ቀጥለው ባሉት የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍሎች ተነግሮናል። <u>ዘፀ 20፥1, ዘዳግ 30፥15, እንደዚሁም 2ኛ ጢሞ. 3፥14 እንመልከት</u>

አዎ <<እምነት>> (ሃይማኖት) ስንል፥ የእግዚአብሔርን የአካል፣ የግብርና የስም ሦስትነት፣ የባሕርይ፣ የህልውና እና የመለኮት (የአምላክነት) አንድነት ጠንቅቆ በመረዳት፣ ለሌላውም ማስረዳት እግዚአብሔር የባሕርይ አምላክ፣ መሐሪና ይቅር ባይ መሆኑን ከልብ በማመን በተግባር ወደ እርሱ መቅረብ፥ ምሕረትን በሚያስገኝ መልክ በመዘጋጀት፣ በምሕረት ሥፍራ በመገኘት ከእርሱ ምሕረትንና ይቅርታን መጠየቅ ማለታችን ነው።

ምክንያቱም ከእግዚአብሔር ሁሉ እንደሚገኝ ያለ ምንም ጥርጥር በልብ አምኖ በተግባር ወደ እግዚአብሔር በመቅረብ ምሕረትንና ይቅርታን ከእግዚአብሔር መጠየቅ፣ ዘለዓለማዊ ሕይወትን መንግሥተ ሰማያትን ከእርሱ መለመን ማለት፡ የእግዚአብሔርን የባሕርይ አምላክነት በተግባር ማረጋገጥ ማለት ነው። እግዚአብሔር አምላካችንም እንደዚህ ሆነን ከቀረብነው በትንቢተ ኤርምያስ፥ <<በዚያን ቀን አድንሃለሁ፥ በምትፈራቸው ሰዎች እጅ አልሰጥህም (አማርኛው ሲቃና በምትፈራቸው ሰዎች እጅ ላይ አልጥልህም) ፈጽሜ አድንሃለሁ>> በማለት በማይሻር ቃሉ በተናገረው መሠረት ሁላችንንም ይምረናል፣ ይቅርንም ይለናልና በመልካም ምግባር የሚገለጽ ትክክለኛ እምነት ሊኖረን ያስፈልጋል፣ በእምነታችን ጸንተንም በንጹሕ ልብ ወደ እርሱ ልንቀርብ ይገባናል። <u>ኤር. 39፥17</u>

<u>እምነት (ሃይማኖት) በምን ይታወቃል? ያልን እንደሆነም መልሱ በመልካም ምግባር (በሥራ) ነው።</u>





አዎ ከዚህ በላይ በሰፊው እንደተገለጸው የእምነት መታወቂያው መልካም ምግባር ሠናይ ሥራ ሲሆን፥ መልካም ምግባር ሠናይ ሥራ የሚባለውም ጾም፣ ጸሎት፣ ምጽዋት፣ ትሕትና፣ ርኅራኄ እና የመሳሰለው እግዚአብሔርንና ሰውን የሚያስደስት መልካም ግብር ሁሉ እንደሆነ ተደጋግሞ ተገልጾአል።

የእነዚህ ሁሉ ዋና ማሠሪያም እውነተኛ ፍቅር እንደሆነ ብዙ ጊዜ ተነግሮናል። በቅዱስ መጽሐፍ በብዙ ክፍል ተጽፎአል። አሁንም በዚሁ ዝግጅት በየክፍሉ ተጠቅሶአል።

ምክንያቱም የጽድቅ ሥራ የሚባሉት ሁሉ በእውነተኛው ፍቅር ሊከናወኑ ስለሚችሉ ነው በብዙ ክፍል የተጠቀሰው እውነተኛ ፍቅር ከሌለ ግን መልካሙን ሥራ መሥራት እንደማይቻል የታወቀ ነው

<u>እምነት (ሃይማኖት)</u> እና መልካም ምግባርም ከተለያዩ ዋጋ ስለሌላቸው እምነት (ሃይማኖት) እና መልካም ምግባር ፈጽመው ሊለያዩ እንደማይችሉ በብዙ ክፍል ተደጋግሞ ተጠቅሶአል።

ስለሆነም እውነተኛውን ፍቅር መሠረት በማድረግ ትክክለኛውን እምነታችን (ሃይማኖታችንን) በመልካም ምግባር መግለጽ ይገባናል ማለት ነው።

<u>በተጨማሪም እነዚህ ጥቅሶችንና ማብራሪያቸውንም እንመልከት፥</u>

<u>1ኛ</u> እግዚአብሔር አስቀድሞ ሰማይንና ምድርን ፈጠረ። <u>ዘፍ. 1፥1</u>

<u>2ኛ</u> ሁሉንም የፈጠረ እግዚአብሔር ነው። <u>ዕብ. 3፥4</u>

<u>3ኛ</u> ሰማያትን የፈጠረ፣ የዘረጋቸውም፥ ምድርንና በውስጧ ያለውንም ያጸና በእርሷ ላይ ለሚኖሩ ሕዝብ እስትንፋስን፣ ለሚሔዱባትም መንፈስን የሚሰጥ አምላክ እግዚአብሔር በጽድቅ ጠርቼሃለሁ ይላል። <u>ኢሳ. 42፥5</u>

<u>4ኛ</u> ሁሉን ለሚችል ለሥልጣንህ አይሳነውምና ቍጡ የሆኑ አንበሶችንና ብዙ ጅቦችን ታመጣባቸው ዘንድ እምነበ አልቦ ዓለምን ለፈጠረች ለሥልጣንህ አይሳናትምና <u>መጽ.ጥበብ. 11፥18።</u>

<u>5ኛ</u> ዓለሙን ሁሉ ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ ፈጠረ።

ኮረብቶችንና ተራሮችንም ፈጽሞ አዘጋጀ ምድርንም በውሃ ላይ አጸናት፣ ባሕርም እንዳትናወጥ በአሸዋ ወሰናት።

እግዚአብሔር በመጀመሪያ ቃሉ ብርሃን ይሁን አለ።
<u>መጽ.መቃ. ቀዳማዊ 27፥1</u>

<u>6ኛ</u> ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ የፈጠረህ እግዚአብሔር አይደለምን? <u>መጽ.መቃ. ቀዳማዊ 7፥2</u>

<u>7ኛ</u> የፈጠራችሁ እግዚአብሔርን የማታውቁ...ወዮላችሁ...
<u>መጽ.መቃ. ካልዕ 7፥1</u>

<u>እነዚህ ቃላት የሁሉም ፍጥረታት ባለቤት እግዚአብሔር መሆኑን ነው የሚያስረዱን።</u>

<u>8ኛ</u> እግዚአብሔርን የማወቅ ጉድለት በልቡናቸው ያለባቸው ሰዎች ሁሉ በእውነት ከንቱ ናቸውና በእነዚህ በሚታዩ ፍጥረቶች በዚህ ዓለም የሚኖር እርሱን ያውቁ ዘንድ ተሳናቸው።

ሥራውንም እያዩ ፈጣሪአቸውን አላወቁም....ፀሓይንና ጨረቃን አይተው የፈጠራቸውን ይወቁ። <u>መጽ ጥበብ 13፥1።</u>

<u>9ኛ</u> እንስሶችን ጠይቅ ያስተምሩሃል፣ የሰማይንም ወፎች ጠይቅ ይነግሩሃል....የእግዚአብሔር እጅ ይህን እንዳደረገ፥

ከእነዚህ ሁሉ ይህን የማያውቅ ማን ነው?
<u>ኢዮብ 12፥7 ጀምሮ በሰፊው እንመለከተው።</u>

<u>10</u> <<ሰማያት ይነግራ ስብሐተ እግዚአብሔር>> ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ፥

የሰማይ ጠፈርም የእጁን ሥራያወራል፣ <u>መዝ. 18፥1</u>

<u>11</u> ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ታይቶ የማይታወቅ እግዚአብሔር ለፍጥረቱ በስነ ፍጥረቱ ይታወቃል። <u>ሮሜ. 1፥19</u>





እግዚአብሔር በፍጥረቱ እንደሚታወቅ ሲገልጽ ነው።

<u>12</u> እግዚአብሔር አምላክ ሙሴን በስድስተኛው ቀን ፍጥረቱን ሁሉ ፈጥሮ እንደጨረሰ፣ በሰባተኛይቱ ቀን እንዳረፈ፣ ከዕለታትም ሁሉ እንደለያት፣ ለሥራውም ሁሉ ምልክት አድርጎ እንዳኖራት ጻፍ አለው።

(ስለ ቀዳሚት ሰንበትም ነው)። <u>መጽ. ኩፋሌ 2፥4።</u>

<u>ስለ ስነ ፍጥረት መጽሐፈ ኩፋሌን ከምዕራፍ 2፥1 ጀምሮ እንመልከት።</u>

<u>13</u> የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው።
<u>መዝ. 110፥10, ምሳ. 1፥7።</u>

እግዚአብሔር ማለት የባሕርይ ስም ሆኖ፥ ትርጉሙ የባሕርይ አምላክ፣ የተፈጥሮ ሁሉ ባለቤት፣ ፈጣሪ፣ ገዥ ማለት ነው።

<u>ይኸውም</u>፥እኔ የአባትህ አምላክ፥ የአብርሃም አምላክ፣ የይስሐቅም አምላክ፣ የያዕቆብም አምላክ ነኝ ብሏል እግዚአብሔር <u>በዘፀ. 3፥6</u>

<u>14</u> በምንም የማይወሰን ዘለዓለማዊ የሆነ የባሕርይ አምላክ እግዚአብሔር በሁሉ አለ።

<u>ይኸውም</u>፥ ነቢዩ ዳዊት ከፊትህስ ወዴት እሸሻለሁ ወደ ሰማይ ብወጣ አንተ በዚያ አለህ፣ ወደ ሲኦልም ብወርድ በዚያ አለህ ብሎታል። <u>መዝ. 138፥7</u>

<u>15</u> እኔ የቅርብ አምላክ ነኝ እንጂ የሩቅ አምላክ አይደለሁም፥ ሰው በስውር ቢሸሸግ አላየውምን? ሰማይንና ምድርን የሞላሁ እኔ አይደለሁምን? ይላል እግዚአብሔር
<u>ኤር. 23፥23።</u>

<u>16</u> አቤቱ ለትውልድ ሁሉ አንተ መጠጊያ ሆንህልን፣ ተራሮች ሳይወለዱ፣ ምድር ዓለምም ሳይሠሩ፥ ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም አንተ ነህ። <u>መዝ. 89፥1, ዮሐ 1፥1</u>

አምላካችን እግዚአብሔር ከሁሉም ፍጥረት አስቀድሞ የነበረ መሆኑን ያመሠጥራል።

አዎ እግዚአብሔር ከዓለምና ከፍጥረት ሁሉ አስቀድሞ የነበረ፣ ያለ፣ የሚኖር ነው።

17 በእግዚአብሔር ያመኑ ሰዎች ፍራትና ድንጋጤ የለባቸውም። መጽ. መቃ.ሣልስ 7፥1

18 በእግዚአብሔር አምኖ ያፈረ ሰው ማን ነው? ለምኖትስ ቸል ያለው ማን ነው? መጽ. መቃ.ሣልስ 7፥3

19 <<ወንሕነሰ አመነ ወአአመርነ ከመ አንተ ውእቱ ክርስቶስ ወልዱ ለእግዚአብሔር ሕያው>>

በግእዝ ነው።

ትርጉሙም፥ እኛስ አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጅ እንደሆንህ አውቀን አምነናል።

ይህ በትርጓሜው መሠረት ተስተካክሎ የተገለጸው ቅዱስ ጴጥሮስ ለጌታችን የተናገረው ቃል ነው። ዮሐ 6፥67 ጀምሮ፥

20 በእምነታችሁ በጎነትን ጨምሩ። 2ኛ ጴጥ 1፥5።

እምነትና ምግባር ስለማይለያዩ እምነታችሁን በመልካም ሥራ ግለጹ ማለቱ ነው።

21 እምነት፣ ተስፋና ፍቅር እነዚህ ሦስቱ ጸንተው ይኖራሉ፥ ከእነዚህም የሚበልጠው ፍቅር ነው። 1ኛ ቆሮ 13፥13።

22 እግዚአብሔር ፍቅር ነውና ፍቅር የሌለው እግዚአብሔርን አያምንም። 1ኛ ዮሐ 4፥7,8 ጀምሮ

እምነት፣ ተስፋና ፍቅር በምሥጢር አንድ ሲሆኑ ከእነርሱም ደግሞ እውነተኛው ፍቅር የበለጠ መሆኑን ነው የሚያረጋግጥልን።

ጥቅሶቹ አንድ አንድ ማስተካከያና ማብራሪያ እየተደረገላቸው ከልዩ ልዩ ክፍል የአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ የተወሰዱ ናቸው።





# ምዕራፍ 17፥

## ሃይማኖት በተለይም ደግሞ የክርስትና እምነት መነሻው፥

የሃይማኖት ምንጭ (መነሻ) በቅዱሳት መጻሕፍት በብዙ ክፍል ከምትጠቀሰው፣ የምድር መካከል በመባልም ከምትታወቀው፥ እግዚአብሔርን የሚያመልኩ፥ የእግዚአብሔር ሕዝብ፥ (የእግዚአብሔር ወገኖች) እንደሆኑ በልዩ ልዩ መንፈሳዊና ታሪካዊ መዛግብት የሚነገርላቸው ሕዝበ እስራኤል ከሚኖሩባት በመካከለኛው ምሥራቅ ከምትገኘው ከኢየሩሳሌም እንደሆነ ለሁላችንም ግልጽ ነው።

ምክንያቱም ኢየሩሳሌም ከልደተ ክርስቶስ በፊት፥ ማለትም እግዚአብሔር ከልደቱ በፊት ጀምሮ በምስጋና የሚታወቅባት፣ የእግዚአብሔር የምስጋና ሀገር የምትባል፥ አበውና የእግዚአብሔር መልእክተኞች ቅዱሳን ነቢያት በዙሪያዋ እየተንቀሳቀሱ ሲያስተምሩባት፣ ትንቢት ሲናገሩባት የነበረች፣ ብዙ ቅዱሳት መጻሕፍት የተጻፉባት ከመሆኗም በተጨማሪ፥ መዝሙረኛው ነቢይ ዳዊት የዘመረው መዝሙር በግእዙ ሲጠቀስ፥ <<እግዚአብሔርሰ ንጉሥ ውእቱ እምቅድመ ዓለም፥ ወገብረ መድኃኒተ በማዕከለ ምድር>>
ትርጉሙ፥ እግዚአብሔርስ ከዓለም (ከፍጥረት ሁሉ) አስቀድሞ ንጉሥ ነው፣ <<በምድርም መካከል (በኢየሩሳሌም) መድኃኒትን አደረገ>> በማለት በመዝ 73፥12። አስቀድሞ ትንቢቱን በመናገር ምሥጢሩን ያመሠጠረባት፥ በኋላ ጊዜው ሲደርስም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ ልዩ ልዩ አምላካዊ ሥራውን ሲሠራባት የነበረ፣ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ለፍጥረቱ ሁሉ ሕይወትን፣ ለመላ ዓለምም ፍጹም ሰላምን ለመስጠት የመረጣት፣ ቅዱሳን ሐዋርያትን ከተለያየ አካባቢ ጠርቶ በክህነታዊ መዓርግ (ሹመት) እየሾመ ስልዩ ልዩ መንፈሳዊ አገልግሎት ያሠማራባት፣ በመጨረሻ ጊዜም የፈጠረውን ፍጥረት የሚያስናብትባት የምድር መካከል ናት።

አዎ ኢየሩሳሌም የእግዚአብሔር ተከታዮችና አገልጋዮች ሐዋርያት፣ እንዲዚሁም በእነእርሱ እግር የተተኩ የእነእርሱ ተከታዮች የሆኑ አርድእት፣ (ተማሪዎች) ሊቃውንትም ሁሉ

መንፈሳዊ ተልዕኮአችውን የሚጀምሩባት ከሌሎች ሀገሮች ይልቅ በልዩ መልክ የተመረጠች የሕይወት መስሚ፣ የሃይማኖትና የታሪክ ሀገር መሆኗ የታወቀ ነው። <u>መዝ 73÷12 ትርጓሜውንም እንመልከተው።</u> የክርስትና እምነትም ከኢየሩሳሌም ተነሥቶ ነው ከክርስቶስ ዕርገት በኋላ በክርስቶስ ተከታዮች ቅዱሳን ሐዋርያት አማካይነት ለመላ ዓለም የተዳረሰው ቅዱሳን ሐዋርያት ፈጣሪአቸው ኢየሱስ ክርስቶስን እየተከተሉ፣ ከእርሱ በቀጥታ የተቀበሉትን ንጹሕን ቃለ ወንጌል (የወንጌል ትምህርት) የዓለሙን መከራ በመቻል ዓለምን ዞረው ካስተማሩ በኋላ በልዩ ልዩ ተጋድሎ ቢያልፋም፥ ሃይማኖት በተለይም ደግሞ የክርስትና እምነትና ሥርዓቱ ሁሉ በእነእርሱ ተከታዮች አርድእትና (ተማሪዎቻቸው) አበው ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን አማካይነት እየተስፋፋና እየተጠናከረ ቀጥሏል።

## <u>ክፍል 48÷</u>

## <u>እምነት (ሃይማኖት) በኢትዮጵያ÷</u>

የክርስትና ደሴት በመባል የምትታወቀው ኢትዮጵያ ሀገራችን ማንም አስተማሪና ምንም ጽሕፈት ካልነበረበት ጊዜ ጀምራና (በሕገ ልቡና) በዘመነ ኦሪት፥ (ከክርስቶስ ልደት በፊትም) እግዚአብሔርን የምታመልክ፣ ብሉይ ኪዳንን የተቀበለች የእምነት ሀገር እንደሆነች ቅዱሳት መጻሕፍትና በልዩ ልዩ ምሁራን የተዘገቡት የታሪክ መዛግብት የሚያስረዱ ከመሆናቸውም በተጨማሪ፥ እስከ አሁን ድረስ በሀገራችን ውስጥ እየተካሔደ የሚገኘው ሃይማኖታዊ ሥርዓትና ባህላዊ ልማድም ይህን ይጠቁማል።

<u>ለምሳሌ÷</u>

<u>ሀ</u> በብሉይ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት እንዳይበሉ ተለይተው የተከለከሉ እንስሳት፥

<u>ለ</u> ቀዳሚት ሰንበትን ጨምሮ የበዐላትና የታቦታት አከባበር፣

<u>ሐ</u> የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት፣

<u>መ</u> የአገልጋዮች አለባበስና ሥነ ሥርዓቱ፥

<u>ሠ</u> ጾም፣ ግዝረትና የመሳሰለው ሁሉ፥
<u>(ፍትሐ መንፈሳዊ { ፍታ ነገሥት} እንመልከት)</u>





እንደዚሁም ደግሞ በግብረ ሐዋርያት (በሐዋርያት ሥራ) 8÷26 ጀምሮ እንደምንመለከተው ህንደኬ የተባለች የኢትዮጵያ ንግሥት አዛዥ የነበረ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ በ34 ዓመተ ምሕረት ወደ ኢየሩሳሌም የሔደው፥ ቅዱሳት መካናትን ለመጎብኘት፣ ለመጸለይ፣ ለመስገድ፣ ሃይማኖትን ለማስፋፋት ለመማርና ለመመራመር ስለሆነ ኢትዮጵያ ሀገራችን ከዚያም በፊት የእምነት ሀገር እንደነበረች ያስረዳናል።

ምክንያቱም ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ሃይማኖታዊ በመሆኑ ነው የሃይማኖትን ሥራ ለመሥራት ከሀገሩ ከኢትዮጵያ ወደ ኢየሩሳሌም የሔደው። <u>ግብ ሐዋ (የሐ ሥራ) 8÷26 እንመልከት።</u>

## <u>ምዕራፍ 18÷</u>

## <u>ክርስትና (ጥምቀተ ክርስትና)</u>

ክርስትና ማለት በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም ተጠምቆ ስመ ክርስትናን መቀበል ክርስቲያናዊ የክርስቶስ ወገን መባል፥ የመንፈስ ቅዱስ ልጅ መሆን ማለት እንደሆነ በቦታው ተገልጿል።

አዎ በዚሁ መጽሐፍ ጥምቀት በሚል ክፍል በሰፊው እንደተገለጸው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ከውሃና ከመንፈስ ቅዱስ (ከአብራከ መንፈስ ቅዱስ ከማኅፀነ ዮርዳኖስ) ካልተወለደ፥ <u>ማለትም</u> እችን ልጅነት የምታሰጠውን ጥምቀት በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም በውሃ ካልተጠመቀ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ልጅ እንደማይባልና ወደ መንግሥተ እግዚአብሔር (ወደ መንግሥተ ሰማያትም) ፈጽሞ መግባት እንደማይችል፥ ፍጹም ድኅነትና ፍጹም ሕይወትም እንደማይኖረው በማይለወጥ ቃሉ የነገረን ሲሆን÷

በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ አምኖ የተጠመቀ ግን የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ልጅ ይባላል።

በእግዚአብሔር ማኅበር ገብቶም በክርስቶስ አንድነት ይኖራል ማለት ነው። <u>ማር 16÷16, ዮሐ 3÷5። እንመልከት።</u>

<u>ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም በገላትያ ምዕ 3÷27</u> መልእክቱ፥

በእምነት በኩል ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጆች ስለ ሆናችሁ ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ክርስቶስን ለብሳችኋልና በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁ ማለቱ+ በካህኑ አማካይነት በመንፈስ ቅዱስ ስም በውሃ የምንጠመቀው ጥምቀት ከማኅፀነ ዮርዳኖስ ከአብራከ መንፈስ ቅዱስ በሐዲስ ልደት ተወልደን የእግዚአብሔር ልጆች የምንባልበት+ ስመ ክርስትናን የምናገኝበት፣ የክርስቶስ ወገኖች፣ ክርስቶሳውያን፣ ክርስቲያኖች መሆናችንን የምንታወቅበት ልዩ ስጦታችን መሆኑን ነው የሚያረጋግጥልን።

## <u>ክፍል 49</u>፥

## <u>ክርስትና (ጥምቀተ ክርስትና) በኢትዮጵያ+</u>

ቅዱሳት መጻሕፍት+ በተለይም ደግሞ ከላይ ከፍ ብሉ የተጠቀሰው <u>የሐዋርያት ሥራ 8+26</u> እንደሚያስረዳን የክርስትና እምነት ወደ ኢትዮጵያ ሀገራችን የገባው ከልደተ ክርስቶስ በኋላ <u>በ34 ዓ ም መሆኑ ነው። (ጌታችን ባረገ በ14ኛው ዓመቱም ይባላል)</u>

<u>ይኸውም</u> ፊልጶስ ባጠመቀው ከዚህ ከፍ ብሉ በተጠቀሰው ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ አማካይነት ሲሆን+ ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ የሃይማኖትን ሥርዓት አከናውኖ ከኢየሩሳሌም ወደ ሀገሩ ወደ ኢትዮጵያ እንደተመለሰ ክርስትናን ለሀገሩ ሕዝብ እንዳስተዋወቀና በኋላም ከ328 እስከ 340 ዓ ም አካባቢ በግብፅ ሊቀ ጳጳሳት (ፓትርያርክ) አባ አትናቴዎስ ተሾሞ የኢትዮጵያ የመጀመሪያ ጳጳስ (አቡን) የሆነው ፍሬ ምናጦስ (አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን የተባለው) ሥርዓተ ክርስትናውን ከ350 ዓ ም ጀምሮ በመላዋ የኢትዮጵያ ሀገራችን አካባቢ በትምህርትና በተግባር በይፋ እንዳስፋፋው በብዙ የታሪክ መጻሕፍት ተዘግቦ ይገኛል።

ፍሬ ምናጦስ በአብርሃና አጽብሓ ዘመነ መንግሥት ጊዜ ስለ ሃይማኖት ሥርዓት በግብፅ (እስክንድርያ) ከሃይማኖት መሪዎች ጋር እንዲወያይ ከአክሱም ቤተ መንግሥት የተላከው በ328 ዓ ም ገደማ ሲሆን+ በ325 ዓ ም ወልድ ፍጡር በመለኮቱ በማለት የተነሣ የመጀመሪያ ከሐዲ አርዮስ አፍሪካውያን (ግብፃውያን) ብፁዓን አባቶች አባ እለእስክንድሮስና አባ አትናቴዎስ በተገኙበት ክርክር ተረትቶ የተወገዘበት የኒቅያ ጉባኤ በሚካሔድባቸው ዓመታትና ወቅቶች መሆኑ ነው።





ፍሬ ምናጦስ ከአባ እለእስክንድሮስ ሞት በኋላ በምትኩ በተቀመጠው በአባ አትናቴዎስ የጵጵስናን ክህነታዊና አባታዊ መዓርግ ተሹሞ ወደ ኢትዮጵያ በተመለሰ ጊዜ ሥርዓተ ክርስትናን፣ ትምህርተ ወንጌልን፣ ሥርዓተ ቍርባንና ግብረ ክህነትን (የክህነት አገልግሎትን) በመላዋ ኢትዮጵያ እንደ አስፋፋና መንፈሳዊውን እንቅስቃሴ ሁሉ በሚገባ እንዳጠናከረ ይታወቃል።

ዲያቆናትንና ቀሳውስትንም በአንብሮተ እድ እየሾመ በልዩ ልዩ መንፈሳዊ አገልግሎት ላይ መድቧል። ከኢትዮጵያውያን ምሁራን ጋር በመሆን የሳባውያን ፊደላት ለተጠቃሚዎች በሚያመች መልኩ እንዲዘጋጁ፤ ቅዱሳት መጻሕፍትም ከሱርስት፣ ከዕብራይስጥና ከፅርዕ ቋንቋ ወደ ግእዝ ቋንቋ እንዲተረጉሙ አድርጓል። በ350 ዓ ም ገደማ ክርስትና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሃይማኖት ሆነ ማለት ነው።

ስለዚህም ፍሬ ምናጦስ በኢትዮጵያ የነበረውን ልዩ የሆነ መንፈሳዊ ብርሃንን ስለ አንፀባረቀ በመልካም መንፈሳዊ አገልግሎቱና በሃይማኖታዊ አባትነቱ+ በትጋቱና በሥራው ሁሉ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ትልቅ ተወዳጅነትንና የላቀ ክብርን <u>አግኝቶ+ <<አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን>> በሚል ስም ሊጠራ ችሏል።</u>

(የሰላም አባት፣ ብርሃንን የሚገልጽ፣ ልዩ የሆነ መንፈሳዊ አባትና ሐዋርያ) ለማለት ነው።

### << ምንጭ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ>>
### በብፁዕ አቡነ ጎርጎሬዎስ ሊቀ ጳጳስ

ይህ ሲባል ግን አባ ሰላማ በመንፈሳዊ አባትነቱና በሃይማኖታዊ መሪነቱ መሠረት በሀገራችን የነበረው የክርስትና እምነት በበለጠ እንዲስፋፋ የበኩሉን ጥረት አደረገ ለማለት ነው እንጂ ከላይ በሰፊው እንደተገለጸው ኢትዮጵያ ሀገራችን ከአባ ሰላማ በፊት፤ ከጥንቱም የእምነትና የክርስትና ሀገር ናት።

ስለዚህም መንፈሳዊ ታሪኩ አባ ሰላማ ኢትዮጵያን በሃይማኖት አቀናት ወይም የክርስትናን እምነት ወደ ኢትዮጵያ አመጣ ማለት እንዳልሆነ ሊታወቅ የሚገባው ይመስለኛል።

<u>ትርፍ አስተያየት ነው።</u>

አብ የፍጥረታት ሁሉ ፈጣሪ፣ የአምልኮትና የስግደት ባለቤት መሆኑን በጉባኤው ፊት ተከራክረው ረቱት።

ከስሕተቱ አልመለስምስለ አለም አውግዘው ከሃይማኖታዊ ማኅበራቸው ለዩት።

እ.ኢትዮ.እቆ. በ3ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በ317 ዓ. ም ይላል። የሉሌ መልእኩ 2ኛ እትም ገጽ 75።

## ክፍል 51፥

## ጉባኤ ቊስጥንጥንያ ስለ መቅዶንዮስ፥

2ኛ ከአርዮስ ቀጥሎ መቅዶንዮስ በ381 ዓ ም መንፈስ ቅዱስ ሕጹጽ ነው፥ ማለትም ከሦስቱ አካላት ከአብ፣ ከወልድና ከመንፈስ ቅዱስ አንዱ (መንፈስ ቅዱስ) ሕጹጽ ነው (ከአብና ከወልድ ያንሳል) አካል የለውም በማለት በቊስጥንጥኒያ አካባቢ ተነሣ በ150 ሊቃውንት ተረታ።

ይህም ከክሕደቱ አልመለስ ስለ አለ እንደ አርዮስ ተወገዘ።

እ.ኢትዮ.እቆ. በ3ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በ373 ዓ. ም ይላል። የሉሌ መልእኩ 2ኛ እትም ገጽ 75።

## ክፍል 52፥

## ጉባኤ ኤፌሶን ስለ ንስጥሮስ፥

3ኛ ከመቅዶንዮስ ቀጥሎ ንስጥሮስ የተባለ የቊስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳስ የነበረ ሰው በ431 ዓ ም መለኮትንና ሥጋን ነጣጥሎ ባሕርይንና አካልን ከፋፍሎ የሰበከ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት አካል ሁለት ባሕርይ ነው። ማለትም ከእመቤታችን ሥጋን በነሣ ጊዜ አካሉ ሁለት ሆነ።

ይኸውም በአንዱ አካሉ የእግዚአብሔር አብ ልጅ ሲሆን በአንዱ አካሉ ደግሞ የማርያም ልጅ ነው። አምላክ ከሰው ሊወለድ ስለ ማይችል ከድንግል ማርያም የተወለደው ዕሩቅ ብእሲ፥ እንደ እኛ ተራ ፍጡር ሰው ሲሆን በዮርዳኖስ ወንዝ በሚጠመቅበት ጊዜ ቃል ይህ የምወደው ልጄ ነው ብሎ ስለ አደረበት አምላክነትን አገኘ እንጂ ከዚያ በፊትስ አምላክ አልነበረም አለ።

በእርሱ አባባል ድንግል ማርያም የተራ ሰው እንጂ የአምላክ እናት አይደለችም ማለት ነው።





ስለ ሆነም በኤፌሶን ከተማ 200 ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንና አባቶች ሊቃነ ጳጳሳት የተገኙበት ጉባኤ ተደርጎ በውይይቱ አፈረ በክርክሩ ተረታ።

ይህም ተው ተሳስተሃልና ተመለስ ቢባል እንቢ አልመለስም ስለ አለ እንደመሰሎቹ ተወግዞ ከእውነተኛይቱ የሃይማኖት ኅብረት ተለየ።

ምንም እንኳን አንድ አንድ የተለያየ አመለካከት ሊኖር እንደሚችል ቢገመትም ይፋ የሆነ የሃይማኖት ክፍፍል ግን ስለ አልነበረ እስከዚህ ጊዜ ድረስ የመላው ዓለም ቤተ ክርስቲያን በአንድነት እየተጓዘች መምጣቷን ከታሪኩ እንረዳለን ማለት ነው።

እ.ኢትዮ.እቆ. በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በ423 ዓ. ም ይላል። የሉሌ መልእኩ 2ኛ እትም ገጽ 75።

## ክፍል 53፥

## ስለ ልዮን፥

4ኛ ከዚህ በኋላ በ451 ዓ ም ገደማ ልዮን የተባለ የሮማው ፓፓ የነበረ መርቅያንና ብርክልያን በተባሉት ኃያላን ገዥዎች ጎን ተጠግቶ ቅድም የተጠቀሰውን ሁለት ባሕርይ የሚለውን የንስጥሮስን ክሕደት በኬልቄዶንና አካባቢዋ እንዲስፋፋ ጥረት አደረገ።

መልእክተኞችንም ወደ ሃይማኖት ጉባኤው ልኮ ግርግርን አስነሣ።

የገዥዎቹን ዱላ የፈሩና አድር ባዮቹ ትምህርቱን ተቀብለው በተግባር ላይ ሲያውሉት እንደ እነዲዮስቆሮስ ያሉት ጠንካራ መንፈስ ያላቸው አባቶች ግን በኤፌሶን ጉባኤ የተካሔደውን ምሥጢር መሠረት በማድረግ የክሕደት ትምህርቱን ነቀፉ።

በአርሜኒያ፣ በሶርያ፣ በህንድና በመሳሰሉት የምሥራቅ ሀገራት አብያተ ክርስቲያናት የሚገኙት ሊቃውንትና የቤተ ክርስቲያን አባቶችም እነዲዮስቆሮስን በመከተል የልዮንን ክሕደት ተቃወሙ።

የስሕተት ትምህርቱ እንዲታረምም የየበኩላቸውን አስተውጽኦ አደረጉ።

## ክፍል 56፥

## ስለ አድቨንቲስት፥

7ኛ የአድቨንቲስት እምነትም በ18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ዊልያም ሚለር በተባለው አሜሪካዊ አማካይነት ተመሥርቶ በብዙ አካባቢ እንደ ተስፋፋ ይታወቃል።

አድቨንቲስት ማለት ክርስቶስ ነገ ከነገ ወዲያ ይመጣል እየተባለ የሚሰበክበት አስደንጋጭ እምነት እንደሆነም ይነገራል።

የአድቨንቲስት እምነት በውስጡ ብዙ ክፍፍል አለበት ይባላል።

ከእነእርሱም መካከል ኮንሰርቫቲቭና ኢቫንጀሊካል የሚባሉ ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፥ እንደዚሁም ሰንበት ቀዳሚት እንጂ የአይሁድ አይደለችም የሚሉ ዘሰበንዝ ደይ፣ አድቨንቲስት የሚባሉና ሌሎችም ይህን በመቃወም፣ የሰው ነፍስ እስከ ክርስቶስ ምጽአት ድረስ በመቃብር ውስጥ እንደምትቆይ የሚያምኑ እንደሚገኙበት ይነገራል።

## ክፍል 57፥

## ስለ ጆሆባ ዊትነስ (የየሆባ ምስክሮች ነን ባዮች) {የመጽሐፍ ቅዱስ አጥኒዎች}

8ኛ ጆሆባ ዊትነስ የተባለው እምነት ደግሞ እ እ አቆጣጠር በ1870 ዓ ም አሜሪካ ውስጥ ቻርልስ ራስል በተባለው አሜሪካዊ እንደ ተቋቋመ ይታወቃል።

ይህ እምነት ከአርዮስና ከመቅደንዮስ የእምነት አመለካከት ጋር ተቀራራቢነት እንዳለውና የእምነቱ ተከታዮችም በኢሳ ምዕራፍ 43፥10 የሚገኘውንና የመሳሰሉትንም የቅዱስ መጽሐፍ ጥሬ ቃላትን እየቀነፃፀሉ እየያዙ የይሖዋ ምስክሮች የተባልን እኛ ነን በማለት ሁለት ሁለት እየሆኑ በእየተቋሙ፣ በየት/ቤቱ፥

በየሥፍራውና በየመንገዱ እየተዘዋወሩ፥ እንደዚሁም የግለ ሰቦችን ቤት እያንኳኩ ጽሑፋቸውን በማሰራጨት ብዙ የዋሆችን





ለማጥመድ እንደሚሞክሩና በእየጊዜው በተለያዩ ቋንቋዎች እያሳተሙም በብዙ ሚልዮን የሚቆጠር የማደናገሪያ ጽሑፋቸውን ለመላው ዓለም እንደሚበትኑ ይታወቃል።

ይህ እንቅስቃሴ አሁንም ለሁላችን እያጋጠመን ያለ በተግባር የምናየው ሐቅ ስለ ሆነ ምንም አያጠያይቅም።

## ክፍል 58፥

## ስለ በሐሁላ፥

9ኛ መሥራቹ ዓሊ መሓመድ የሚባል ግለ ሰብ እንደሆነ የሚገለጸው፥ የእምነት ቸለልትነት አለው (በእምነቱ ቸለልተኛ ነው) የሚባለው በሐሁላ የተባለ የእምነት ድርጅት ደግሞ በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ላይ እንደተቋቋመ ይታወቃል።

የዚህን እምነት አራማጆች ስለ እምነት ጥንቃቄን ማድረግ፣ ብዙ ማሰብና መከራከር ተገቢ አይደለም በማለት፣ ለአሁኑ ትውልድ ኢየሱስም ሆነ መሓመድ አላስፈላጊ መሆናቸውን እንደሚገልጹ ይነገራል።

የበሐሁላ እምነት ተከታዮች ከሁሉም የእምነት ዓይነቶች እያዩ ይህ ነው የሚሻል ብለው የሚያምኑበትን ብቻ እንደ አስፈላጊነቱ እያውጣጡ በመውሰድ እንደሚያራምዱትም ይገለጻል።

በሐሁላ ማለት ስብሐተ እግዚአብሔር (የእግዚአብሔር ምስጋና) ማለት ነው።

እንግዲህ እስከ አሁን ድረስ በከፍተኛ እንቅስቃሴአቸው ከታወቁት የእምነት ድርጅቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ እነዚህ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ሲሆኑ፥ አሁን በዐጭሩ ለመግለጽ የማይመቹ በየጊዜው የሚመሠረቱ ከ22 ሺሕ በላይ የሚሆኑ በየበኩላቸው እኛ ብቻ ነን ትክክለኞች የሚሉ የተለያዩ የእምነት ድርጅቶች በዓለም ውስጥ እንዳሉ ይነገራል።

እነዚህ የእምነት ድርጅቶች በየጊዜው በቴክኖሎጂ እድገትና በሳይንሳዊ ፍልስፍና እንቅስቃሴ ላይ እየተመሠረቱ፥ አሁንም በልዩ ልዩ አመለካከት እየተከፋፈሉ በመቀጠል ላይ ስለ ሆኑ

መጀመሪያቸው እንጂ ወዴት እንደሚሔዱና የትም እንደሚደርሱ መጨረሻቸው አይታወቅም።

እኛ ኢትዮጵያውያን ግን ከ3 ሺሕ ዓመት ብቻ ሳይሆን፥ ከዚያ በፊት፥ አስቀድሞም ቢሆን እግዚአብሔርን በእምነት ያሳወቅንበት፣ ከእግዚአብሔር ተለይተን የኖርንበት ዘመን ስለሌለብንና አዲስ አማኞች ስለ አልሆን ማንም አስተማሪና ምንም መጻሕፍት ባልነበሩበት ዘመንም ፈጣሪኣችን እግዚአብሔርን እያመለክንና እያመሰገን የኖርን ነን።

አዎ እኛ ከ34 ዓ ም ጀምሮም ጥምቀተ ክርስትናን የተቀበልን፤ ምን ጊዜም የማይለዋወጥ፣ የማይሸራረፍ በቀደምት አበውና በቅዱሳን ሐዋርያት የተመሠረተ፥ በመልካም ምግባር፥ በሠናይ ሥራ የሚገለጽ ትክክለኛ እምነት ያለን ከመሆናችንም በላይ በክርስቶስ ደም በጸናች ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሥር የምንገኝ ሕዝበ ክርስቲያን ስለ ሆን፥ አሁን ክርስቶስን ተቀበልን በሚሉ አዲስ አማኞች የማታለያ ዘዴ ልንታለልና ልንደናገር አንችልም።

ግብረ ሐዋርያት (የሐዋርያት ሥራ) 8፥26 እንመልከት።

አዎ እኛ የክርስቶስ ወገኖች እውነተኞች ክርስቲያኖች ነን ስንል በእውነተኛው እምነታችን ጸንተን በቅዱሳን ሐዋርያት አማካይነት በቀጥታ ከጌታችን የተገኘውን በእውነተኞች ቅዱሳን አባቶቻችንና በቅዱሳት መጻሕፍት በትውፊት የተረከብነውን ሃይማኖታችንን ጥንታዊ ሥርዓቱንና መንፈሳዊ ባህሉን በመጠበቅ፣ በማስጠበቅ፣

መልካም ምግባር ሠናይ ሥራ በሚባለው በጾም በጸሎት በምጽዋት በትሕትና፣ በሰላም፣ በርኅራኄ፣ በአንድነትና በፍቅር ስለምንገልጽ ነው።

የሃይማኖት ትርጉሙ መልካም ሥራ እንደመሆኑ መጠን፥ ሃይማኖትን ከምግባር ጋር መያዝ ማለትም ይህ ነው።

ለዚህ እውነተኛ ሃይማኖታችን ማስፈጸሚያ የሚሆንም ቅዱሳት መጻሕፍትን እየጠቀሰ የሚያስረዳ፥ ቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረት አድርጎ የተመደበ ሃይማኖታዊ ቀኖና አለን።

እዚህ ላይ ግን ከሁሉም በፊት ስለ ሃይማኖትና ስለ ሃይማኖታዊ ቀኖና ምሥጢር በተጣራ መንገድ ለይቶ ማወቅ ተገቢ ይመስለኛል።





# ምዕራፍ 21፥

# ሃይማኖት ወይም እምነት በሌላ አጠራርም ዶግማ ማለት፥

አዎ በዐጭሩ ለማስቀመጥ ሃይማኖት ወይም እምነት በሌላ አጠራርም ዶግማ የሚባለው የእግዚአብሔርን አንድነትንና ሦስትነትን ጠንቅቆ በማወቅ፣ አንድነቱንና ሦስትነቱን ማመን፣ ይኸውም ሥላሴ፥ አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ተብለው በመጠራት፥ የስም ሦስትነት ያላቸው፥ ማለትም፥ በስም፣ በግብር፣ በአካል፥ ሦስት ሲሆኑ፥ በባሕርይ፣ በመለኮት፣ (በአምላካዊ ሥራ) በሥልጣን፣ በህልውና፣ ፍጥረትን ሁሉ በመፍጠርና በመስለው ግን አንድ ናቸው፤ አሐዱ እግዚእ፥ አንድ ጌታ፣ አንድ እግዚአብሔር።

ፍጹም አምላክ የሆነ ክርስቶስ በሥጋዌው (ፍጹም ሰው በመሆኑ) ምሥጢር፥ አንድ አካል፣ አንድ ባሕርይ፣ አንድ እግዚአብሔር እንደሆነ፥ <<ዘሠረፀ እምአብ ዘእንበለ እም>> ተዋሕዶቱ አምላካዊ ባሕርይ የሆነ ክርስቶስ ቅድመ ዓለም (ከዓለም ፍጥረት በፊት) ያለ እናት ከባሕርይ አባቱ፣ ከባሕርይ ሕይወቱ ከእግዚአብሔር አብ እንደተወለደ፥ <<ወዘተወልደ እማርያም እምቅድስት ድንግል ዘእንበለ ዘርዓ ብእሲ>> በኋላም ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ያለ አባት፣ ያለ ዘርዓ ብእሲ (ካለ ወንድ ዘር) በኅቱም ድንግልና ተፀንሶ፣ በኅቱም ድንግልና የተወለደ፥ ወልደ አብ፣ ወልደ ማርያም (የአብ ልጅ፣ የማርያም ልጅ) ተብሎ በተዋሕዶ የከበረ መሆኑን ማመን፥ እግዚአብሔር የባሕርይ አምላክ፣ መሐሪ፣ ይቅር ባይ ስለ ሆነ በደላችንን ሁሉ ይቅር ብሎናል፣ ከሰማዩ ሰማያት ወርዶ፣ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ፣ በቀራንዮ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ አድኖናል ብሎ አምኖ ማሳመን፥ ይህ ኀብስት ጌታችን ሥጋዩን የበላ ደሜንም የጠጣ ለዘለዓለም ሕያው ሆኖ ይኖራል፣ ባለው መሠረት ስለ ዓለም ድኅነት፣ ስለ ስርየተ ኃጢአት፣ ስለ እኛ ዘለዓለማዊ ሕይወት በቀራንዮ የተፈተተ ቅዱስ ሥጋ ነው።

ወይኑም የእኛን ኃጢአት ለማስወገድ በቀራንዮ የፈሰሰ የክርስቶስ ክቡር ደም ነው። ፍጹም መድኃኒታችን ነው፤ ከዚህ በስተቀር ፍጹም ድኅነት የለም ብሎ ከልብ አምኖ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር

# ምዕራፍ 22፥

## ስለ ታቦትና መሠረታዊ ምሥጢሩ ዐጭር ማብራሪያ

ታቦት ቤተ አደረ ከሚል የግእዝ ግስ የሚገኝ ዘር ነው።

ትርጉሙም ማደሪያ የሚል ሆኖ የእግዚአብሔር ማደሪያ ማለት ነው።

ይኸውም እግዚአብሔር በእርሱ አድሮ የሚመስገንበት፣ ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ የሚፈተትበት፣ የእግዚአብሔር ስም የተጻፈበት ኃይልና ተአምርም የሚገለጽበት ነው።

መሠረታዊ አመጣጡ፣ መንፈሳዊ ምሥጢሩና ትርጉሙም ከዚህ ቀጥሎ በዐጭሩ ተገልጿል።

1ኛ መሠረታዊ አመጣጡ፥

ሀ መጀመሪያ እግዚአብሔር ለሙሴ እንደ ሰጠው፥ በዘፀ 24፥12

ለ ከግራር ዕንጨት እንዲሠራም በእግዚአብሔር የታዘዘ እንደሆነ፥ በዘፀ 25፥5, 37፥1

ሐ ንዋየ ቅድሳቱን የሚሠሩም በእግዚአብሔር የተመረጡ ጠቢባን እንደ ነበሩ፥ በዘፀ 31፥1

መ የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን፥ የእግዚአብሔር ሕግና ትእዛዝ ያለባቸው መጀመሪያ በእግዚአብሔር ለሙሴ የተሰጡት ጽላቶች ወይም ታቦት በእግዚአብሔር የተጻፉና የእግዚአብሔር ድንቅ ሥራ እንደሆኑም፥ በዘፀ 24፥12, እና 32፥15 በሰፊው ተጽፏል።

(ጽላት ማለት የእግዚአብሔር ስም የተጻፈበት ቅዱስ ሠሌዳ ማለት ነው)

2ኛ ታቦቱ ሲሰጠው ከነበረው መፈሳዊ አገልግሎት ውስጥም፥





ሀ የሙሴና የእግዚአብሔር፣ የእግዚአብሔርና የእስራኤል መንፈሳዊ መገናኛ እንደ ነበርና፣

ለ ከጥንቱ ጀምሮ የምስጋናና የቃለ ኪዳን ቅዱስ ንዋይ (መሣሪያ) እንደሆነ፥ በዘፀ 25፥21

ሐ እንዲሁም የእግዚአብሔር ስም የተጻፈበትን ጽላት ወይም ቅዱስ ሠሌዳ የሚባለውን በውስጡ ሲይዝ እንደነበረም በዘፀ 40፥20 ተጠቅሷል።

ጠቅላላውን ታሪኩ 10 ቃላት ካሉበት ከዘፀ 20፥1 ጀምሮ እንመልከት፥ የታቦቱ መንፈሳዊ አግልግሎቱን መስጠትና የሙሴ በታቦቱ አማካይነት ከፈጣሪው ጋር መነጋገር በዘኁልቍ 7፥89 ጀምሮም እናገኛዋለን።

ለታቦት መስገድ እንደሚገባ ኢያሱ 7፥6 ለታቦቱ ክብርና አጀብ ማድረግ፥ መንፈሳዊ መዝሙርንም መዘመር ተገቢ እንደሆነም 2ኛ ሳሙ 6፥14 1ኛ ዜና መዋ 13፥8, 15፥28 ያስረዳናል።

የአሁኑ ታቦትን የሚመለከት መንፈሳዊ ሥርዓታችንም ሁሉ መሠረቱ ከዚህ የተወረሰ እንደሆነ ግልጽ ነው።

ስለ ክብሩ ሕዝቡ ከ2 ሺህ ክንድ በላይ ይርቁ ስለነበር አሁንም ታቦቱን መዳፈር አይገባም ኢያሱ 3፥4፣

የሚዳፈሩት እንደሚቀሰፉም 2ኛ ሳሙ 6፥6 1ኛ ዜና መዋ 13፥9 ጀምሮ እንመልከት።

3ኛ ታቦተ እግዚአብሔር ልዩ ልዩ ተአምራትን ያደርጋል።

ለምሳሌ፥ የዮርዳኖስን ባሕር በመክፈል ታይቷል። ኢያሱ 3፥11 ጀምሮ

የኢያርኮን ግንብ በማፍረስም ኃይሉንና ተአምራቱን ገልጿል። ኢያሱ 6፥6 ታቦተ እግዚአብሔር በካህናት ብቻ መያዝ እንደሚገባውም በኢያ 3፥11, 6፥6 ተዘግቧል።

የእግዚአብሔር ታቦት ካህናት ተሸክመውት በልዩ ልዩ ዝማሬና በዕልልታ ፈጣሪያችን እግዚአብሔርን እያመሰገን ዑደትን ማድረግ ጠቃሚነቱና መሠረታዊ ታሪኩም በኢያሱ 6፥6 እናገኘዋለን።

የእግዚአብሔር ታቦት ከጣዖት የተለየ እንደሆነና በጣዖትም ላይ ኃይልንና ተአምራትን እንደሚያደርግም ተደጋግሞ በተግባር ላይ ታይቷል። 1ኛ ሳሙ 5፥1 ጀምሮ, 2ኛ ቆሮ 6፥16።

የማናቸውንም ምስል ቀርፀህ ለአንተ አታድርግ አትስገድለትም አታምልከውም ተብሎ በእግዚአብሔር የተነገረ ወይም የታዘዘው ደግሞ እግዚአብሔር እንደሆነ ታምኖበት ለሚቀመጥ ምስል፥ ይህ ነው ሁሉን ማድረግ የሚቻለው፥ የባሕርይ አምላክ ተብሎ ለሚመለከው ጣዖት ነው እንጂ እግዚአብሔር ለሚመሰገንበት የእግዚአብሔር ታቦት አይደለም። ዘፀ 20፥4, ዘዳ 4፥15,ኢሳ 40፥18

በጊዜያችን ያለው ታቦትም ምሥጢሩና ሥርዓቱ ከዚህ ተያይዞ የመጣ ሲሆን እንዲሁም እግዚአብሔር የሚመሰገንበት፣ የእግዚአብሔር ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደምም የሚፈተትበት የእግዚአብሔር ስምና ረቂቅ የሆነ ምሥጢራዊ ሥራም ያለበት ነው። ራዕየ ዮሐንስ 1፥17,11፥17።

በሰማይ ያለና በምድር የሚገኘው የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስም የሚነፃፀሩ ሲሆኑ ሁለቱ የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታቦትን በውስጣቸው እንደያዙ፥ ራዕየ ዮሐንስ 11፥19። ይገልጻል። እኛም የፈጣሪያችንን ሕግንና መመሪያን ጠብቀን፥ ትሕትናን፣ የዋህነትን፣ ደግነትንና ይቅር ባይነትን ይዘን በእውነተኛው ፍቅር አንድ ሆነን ለሁሉም ዓለም ሰላም፣ ለእኛ ፍጹም ሕይወት በቀራንዮ በመስቀል ላይ የተፈተተውን የክርስቶስን ቅዱስ ሥጋንና ክቡር ደምን የተቀበልን በመሆናችን፥ የእግዚአብሔርን አንድነቱንና ሦስትነቱን፣ መሐሪነቱን፣ ፍጹም ሕይወትነቱንና መድኃኒትነቱን አምነን ተጠምቀን የተቀበልነው ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ከእኛ ጋር ስለተዋሐደ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደምንባል የታወቀ ነው። 1ኛ ቆሮ 3፥16, 6፥19, 2ኛ ቆሮ 6፥16, ኤፌ 2፥22, 1ኛ ጴጥ 2፥7 እንመልከት።

እንግዲህ ከዚህ በላይ እንደተገለጸው ሃይማኖታችንና መንፈሳዊ ሥርዓታችን እውነተኛውን የእግዚአብሔር መንገድ ይዞ የመጣ ምንም ሳይበረዝ በዚሁ መልክ የተረከብነው አሁንም ትክክለኛውን መሠረቱ ይዞ፣ ሃይማኖታዊ ሥርዓቱንም ጠብቆ ነው እየሔደ ያለው።

ለዚህ ሁሉ ዋና ምንጭና መሠረት የሆኑት የብሉይ ቅዱሳት መጻሕፍትም እንዳልተሻሩ ራሱ ጌታችን ነግሮናል። ማቴ 5፥17





አዎ ቀደምት የእግዚአብሔር ወዳጆች አባቶቻችን እምነታቸውን በአግባቡ ሲፈጽሙ የእግዚአብሔርን የቃል ኪዳን ታቦት ሲያከብሩና ሲንከባከቡ፣ በታቦቱ አማካይነት የተለያየ ድልን ሲያደርጉ ሕገ እግዚአብሔር ለተጻፈበት፣ ስመ እግዚአብሔር ለተቀረፀበት ለታቦቱ ሲሰግዱ እንደነበሩ፥ እግዚአብሔርም በታቦቱ አድሮ ወይም በታቦቱ አማካይነት ልዩ ልዩ ኃይልንና ተአምራትን ሲያደርግ እንደነበር ቅደም ተከተሉን ጠብቆ በመጣው በትክክለኛው የቅዱስ መጽሐፍ ማስረጃ አይተናል። የቤተ ክርስቲያናችንንም ምሥጢር ተረድተናል።

እኛም ቀደም ሲል ከአበው፣ ቅዱሳን ነቢያት፣ በኋላም ከሐዋርያት ጀምሮ እስካለንበት ዘመን የደረሰውን፣ በመንፈሳዊ ትውፊት የተረከብነውን፣ ምንም ያልተቀላቀለበትን ሃማኖታችንንና መንፈሳዊ ባህላችንን መሠረት በማድረግ ሃይማኖታዊ አገልግሎታችንን፣ ስናከናውን ፈጣሪያችን እግዚአብሔርን ስናመሰግን እንኖራለን።

እንኳን አማናዊ የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ለሚፈተትበት የእግዚአብሔር ታቦት፥ ታቦቱ ለሚያርፍበት የእግዚአብሔር እግር ለቆመበት ስሙ ለሚጠራበት ቅዱስ መካን ስንሰግድ፣ መንፈሳዊ ሥርዓቱንም ስንፈጽም፥ አሁን በየደረጃው እንደተመለከትነው የብሉዩንና የሐዲሱን ቅዱስ መጽሐፍ መሠረት በማድረግ ነው እንጂ መናፍቃን እንደሚሉት ዝም ብለን በልማዳዊና ኋላ ቀርነት ባህል እየተጉተትን አይደለንም።

ንዋየ ቅድሳት በመባል የሚታወቁ በቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ የሚገኙት የምስጋና መሳሪያዎችም ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር ሲመሰገንባቸው የነበሩ ሲሆኑ ለእያንዳንዳቸው መሠረታዊ ሥጢር አላቸው። መዝ 131፥7,ሕዝ 46፥2 እንመልከት። ታድያ ግን የእምነታችን ተቃዋሚዎች፣ የሥርዓታችን ተጻራሪዎች የሆኑ በተለያየ ሁኔታ በየጊዜው የሚነሡ መናፍቃንና ተከታዮቻቸው ይህን ትክክለኛውን የጽድቅ መንገድ ባይቀበሉት፣ እያወቁም ሊያቃልሉትና ወደ ጎን ሊተዉት ቢሞክሩ የእነርሱ ችግር ስለ ሆነ የሚጐዱት እነርሱ ብቻ ናቸው።

ሆኖም ግን በተለያየ የማሳሳቻ ዘዴያቸው እንዳያደናግሩን እኛን መስለው ከውስጣችን ገብተውም እንዳይበርዙን ነቃ ብለን ተገቢውን መንፈሳዊ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልገናል።

እንዲሁም ትክክለኛውን ሃይማኖታችንንና ሃይማኖታዊ ሥርዓታችንን፥ መንፈሳዊ ታሪካችንንና፥ ባህላችንንም ሁሉ ከጥንቱ ጠንቅቀን በማወቅ በተማርነው መሠረት መጽናት ይገባናል።

በተጨማሪም ከዚህ ቀጥለው ያሉት ጥቅሶች እንመልከታቸው።

1ኛ አንተ ግን በተማርህበትና በተረዳህበት ጸንተህ ኑር። 2ኛ ጢሞ 3፥14

2ኛ እንግዲህስ ወንድሞች ሆይ ጸንታችሁ ቁሙ በቃላችንም ቢሆን ወይም በመልእክታችን የተማራችሁትን ወግ ያዙ። 2ኛ ተሰ 2፥15

3ኛ የእርሱን ግርማ አይተን እንጂ በብልኃት የተፈጠረውን

ተረት ሳንከተል የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ኃይልንና መምጣትን አስታወቅናችሁ። 2ኛ ጴጥ 1፥16

4ኛ ይህን በመጀመሪያ እወቁ በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደም። 2ኛ ጴጥ 1፥20

5ኛ ከማያምኑ ጋር በማይመች መንገድ አትጠመዱ፤ ጽድቅ ከዓመፅ ጋር ምን ተካፋይነት አለውና፤ ብርሃንም ከጨለማ ጋር ተካፋይነት አለውን ወይስ የሚያምን ከማያምን ጋር ምን ክፍል አለው? የእግዚአብሔር ታቦትንስ በጣዖት ቤት ውስጥ የሚያኖር ማን ነው? እኛ የሕያው የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነንና። 2ኛ ቆሮ 6፥14፥

6ኛ የሚያናውጡአችሁ፤ የክርስቶስንም ወንጌል ሊያጣምሙ የሚወዱ አንድ አንዶች አሉ። ነገር ግን እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ መልአክ፥ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን። አስቀድመን እንዳልን እንዲሁ አሁንም ሁለተኛ እላለሁ ከተቀበላችሁት የተለየውን ማንም ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን። ገላ 1፥7።

7ኛ በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ እርስ በርሳችሁ ተነጋገሩ፥ ለጌታ በልባችሁ ተቀኙና ዘምሩ። ኤፌ 5፥19

8ኛ እርስበርሳችሁ በሰላም ሁኑ፥ ወንድሞች ሆይ እንለምናችኋለን (እንመክራችኋለን) ያለ ሥርዓት የሚሔዱትን ገሥጹአቸው...ሰውን ሁሉ ታገሡ፤ ማንም በሌላው በክፉ ፈንታ ክፉ እንዳይመልስ ተጠንቀቁ፤ ነገር ግን...ሁሉ ጊዜ ለሁሉም መልካሙን ለማድረግ ትጉ ሁሉ ጊዜ ደስ ይበላችሁ፤ ሳታቋርጡ ጸልዩ፤ በሁሉ አመስግኑ። 1ኛ ተሰ 5፥13።





## ምዕራፍ 23፥

## እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ፥

የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ፥ ከልደቷ እስከ ዕርገቷ ያለው ምሥጢር በዐጭሩ ሲገለጽ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ይመስላል።

### መግለጫና ማብራሪያ፥

<<ተፈሥሒ ፍሥሕት ኦ ምልዕተ ጸጋ እግዚአብሔር ምስሌኪ>> ምልዕተ ክብር ቅድስት ድንግል ማርያም ሆይ እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነውና፥ ደስ ይበልሽ። እግዚአብሔር ከሥጋሽ ሥጋን፤ ከነፍስሽም ነፍስን ነሥቶ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ይሆናል። (ከአንቺ, ካንቺ ይወለዳል።)

<<ቃሉ ከሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 1፥28 የተወሰደ ሲሆን፥ ምሥጢሩም በአበው ትርጓሜ መሠረት ሲብራራ ነው>>።

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ ከሌላው ፍጥረት በተለየ መልኩ ከኀልዮም ከነቢርም ሁሉ ድንግል፤ ንጽሕት፤ ፍጽምት ናት።

ይኸውም፥ ከሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን አባቶቻችንና ከትርጓሜ ቅዱሳት መጻሕፍት ትክክለኛ ምሥጢር እንደምንገነዘበው፤ ከሴቶች መካከል ተለይታ መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የሌለባት ናት።

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በአዳምና በሔዋን ከተፈጸመው እግዚአብሔርን የሚያሳዝን ድርጊትና በዚሁም ምክንያት በላያቸው ላይ ወድቆ ጌታችን በመስቀል ተሰቅሎ እስከ ደመሰሰው ድረስ ለትውልድ ሲተላለፍ ከነበረው ከፈጣሪ ከእግዚአብሔር አምላክ የሚያስርቅ (ከፈጣሪ ከሚያሸሽ) መርገምም ሆነ፥ በሔዋንና በዘሯ ላይ ከሚታየው ፃዕረ ወሊድ፤ እንዲሁም ሌላው ሥጋዊ ኀልዮ (ሐሳብ) ሥጋዊ ጠባይዕ (ሥጋዊ ባሕርይ) ሁሉ ፈጽማ ንጽሕት ናት፤ ነውርም ሆነ በዘመናችን ጥንተ አብሶ የሚባለው አላገኛትም፤ ፈጽሞም የለባትም።

እንደዚሁም ከእግዚአብሔር በተቀበለችው የማይሻር የአማላጅነት ቃለ ኪዳን መሠረት በረከተ ሥጋንና በረከተ ነፍስን እያማለደች የምታሰጥ ናት።

አዎ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር ስለሌለ ዓለም ሳይፈጠር በኀሊና አምላክ (ታስባ)የነበረች እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ገና ሳትወለድ ከእናቷ ማኅፀን ሳለች እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ከማንኛውም ነውርና የውርስ ኃጢአት ጠብቆ ከሌሎች ንጹሓን የተለየች ንጽሕት ልዩ አድርጎ ፈጥሯታል።

ይህ በፍጡር ሊለካ የማይቻል፣ የማይመረመር የእግዚአብሔር አምላካዊ ጥበብና አምላካዊ ሥራ ነው።

ምክንያቱም ሌላው ፍጡር ሁሉ ምንም እንኳ ኃጢአትን ከመሥራት የታቀበ ከገቢር (በተግባር ከመፈጸም የተቆጠበ) ንጹሕ ቢሆንም በተፈጥሮአዊ ባሕርዩ እንደእርሷ ስለ አልሆነ ከተፈጥሯዊ ኅልዮ፥ ማለትም በሥጋዊ ጠባይዕ (በሥጋዊ ባሕርዩ) የዓለምን ጊዜያዊ ደስታ ከማሰብ ከቶ ንጹሕ ሊሆን አይችልም።

እርሷ ግን ከኅልዮም ከገቢርም ማለትም በኀሊና (በልብ) ከማሰብም ሆነ በተግባር ከመፈጸም ሁሉ ንጽሕት ፍጽምት ናት።

ሰው ከመወለዱ በፊት በፈጣሪው በእግዚአብሔር ተመርጦ ለልዩ ልዩ ተግባር ሊመደብ እንደሚችል ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚያስረዱን ሁሉ እመቤታችን ገና ሳትወለድ ከእናቷ ማኅፀን ጀምራ በመንፈስ ቅዱስ ከማንኛውም ነውርና የውርስ ኃጢአት ተጠብቃ ለአምላክ እናትነት የተመረጠች ናት።

ይኸውም፥ እግዚአብሔር አምላክ ደጋጎች ሰዎችን አስቀድሞ እንደሚያውቅና ለመልካም ተግባርም በብዙ ክፍል ሊመርጣቸው እንደሚችል እንረዳለን።

ለምሳሌ ኤርምያስን በኆድ ሳልሠራህ አውቄሃለሁ፣ ከማኅፀን ሳትወጣም ቀድሼሃለሁ፣ ለአሕዛብም ነቢይን አድርጌሃለሁ ብሎታል። <u>ኤር 1፥4</u> ይህ ቃል ገና ከእናታችን ማኅፀን ሳለን፣ ከመወለዳችን በፊት አስቀድሞ ምን ዓይነት ባሕርይ እንዳለን በፈጣሪአችን በእግዚአብሔር ዘንድ እንደምንታወቅ፣ ፈጣሪአችን ከማንኛውም ኃጢአት ጠብቆ፣ ባርኮ፣ ቀድሶም ለእርሱ መልካም አገልግሎት፣ ለጽድቅ ሥራ ሊመድበን እንደሚችል ነው የሚያስረዳን

ነቢዩ ዳዊትም አንተ ግን ከኆድ አውጥተኸኛልና በእናቴ ሳለሁም ባንተ ታማንሁ፣ ከማኅፀን ጀምሮ ባንተ ላይ ተጣልሁ፣ ከእናቴ ኆድ ጀምረህ አንተ አምላኬ ነህ ብሉኣል። <u>መዝ 21፥9።</u>





በመዝሙር መቶ ሰላሣ ስምንት ከቍጥር አንድ ጀምሮም <<አቤቱ መረመርኸኝ አወቅኸኝም፣ አንተ መቀመጤንና መነሣቴን አወቅኽ፣ ሓሳቤን ሁሉ ከሩቅ አስተዋልኽ፣ ፍለጋዬን ዕረፍቴን አንተ መረመርኽ፣ መንገዶቼን ሁሉ ቀድመህ አወቅህ ያለ ሲሆን፥

በመዝሙር መቶ ሦስት ከቍጥር ሃያ አራትም አቤቱ ሥራህ እጅግ ነው ሁሉንም በጥበብ አደረግህ>> በማለት የባሕርይ አምላክነቱን በማመሥጠርና በማድነቅ ፈጣሪው እግዚአብሔርን አመስግኗል። <u>መዝ 138፥1, 103፥24።</u>

<u>ነቢይ ዳዊት ስለ ኃጥኣን ሲገልጽም</u> ኃጥኣን ከማኅፀን ጀምረው ተለዩ፣ ከኆድም ጀምረው ሳቱ፣ ሐሰትንም ተናገሩ፣ ቍጣቸው እንደ እባብ መርዝ ነው ይላል። <u>መዝ 57፥3።</u>

ይህ ደግሞ ኃጥኣን ከእናታቸው ማኅፀን ሳሉ ጀምረው ክፎች እንደሆኑ በፈጣሪኣቸው በእግዚአብሔር ዘንድ የታወቁ መሆናቸውን ነው የሚገልጽልን።

አዎ የክሕደት፣ የክፋትና የተንኮል ተግባር አራማጆች የሆኑ መርዘኞች ሰዎች የኃጢኣትና የዓመፃ ጠበቆች መሆናቸው አስቀድመው በእግዚአብሔር ዘንድ ይታወቃሉ።

ስለሆነም በክፋትና በተንኮል ነፋስ የተሞሉ ሰዎች እግዚአብሔርንና ሰውን ሁሉ ሲያሳዝኑ ይኖራሉ፥ ጥራት ካለውና ጸጥ ብሉ ከሚኖረው ባሕረ መለኮት (እውነተኛው እምነት) እየገቡም፣ የኑፋቄንና የክሕደት ማዕበል እያስነሡ በትክክለኛ መንገድ የሚጓዘውን የእግዚአብሔር ሕዝብ ያውካሉ፣ አላስፈላጊውን (ተገቢ ያልሆነውን) ነገር በማንቀሳቀስም አንዱን ከአንዱ ጋር ያጋጫሉ፣ ያልሆነውን እንደሆነ፣ ያልተደረገውንም እንደተደረገ አስመስለውእያወሩ፣ እያስወሩም፤ በአንድነትና በፍቅር የሚኖረውን ሕዝበ እግዚአብሔር ያበጣብጣሉ፣ የቤተ ክርስቲያንና የሕዝበ ክርስትያንን ሰላም ያደፈርሳሉ ማለት ነው።

በእግዚአብሔር አስቀድመው የተመረጡ ሕዝበ እግዚአብሔር ግን የእግዚአብሔር ማደሪያዎች፣ የሕይወት መሪዎች ናቸው፥ እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ነው፥ እነርሱም ከእግዚአብሔር ጋር ሆነው እግዚአብሔር የሚወደውንና ሁሉም ሰው የሚጠቀምበትን መልካም ሥራ ይሠራሉ፣ ሰላማውያን በመሆናቸው ሁል ጊዜ የሰላምን መልእክት ሲያስተላልፉ ይኖራሉ ማለት ነው። <u>መዝሙረ ዳዊት 21፥1, 57፥3, 88፥10, ሄኖክ 4፥15, ኤር 1፥4 እንመልከት።</u>

በመሆኑም አብርሃምንና ሣራን፣ ዘካርያስንና ኤልሳቤጥን ሌሎችንም ለመልካም ሥራ የመረጠ፣ በዕድሜ ከሸመገሉ በኋላም ደጋጎች ልጆችን እንዲወልዱ ያደረገ እግዚአብሔር የሚሳነው ነገር ስለሌለ እመቤታችንን በድንጋሌ ሥጋ፣ በድንጋሌ ኅሊና ጠብቆ ለዚሁ ደረጃ አብቅቷታል። <u>ዘፍጥ 17፥1, 18፥14 ጀምሮ።</u>

ስለዚህም እመቤታችን አስቀድማ በአምላክ ኅሊና የነበረች፣ ገና ሳትወለድ ከእናቷ ማኅፀን ሳለች እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በአዳምና በሔዋን ምክንያት የመጣውና ለመላው ትውልድ ሲተላለፍ ከነበረው መርገምና የውርስ ኃጢአት ሁሉ የጠበቃት፥ ሰማይና ምድር የማይችሉትን የባሕርይ አምላክ ባጭር ቁመቷ፣ በጠባብ ደረቷ እንድትሸከም፥ (የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ እንድትሆን) በአማላጅነቷ ለሚያምን፣ በቃል ኪዳኗም ለሚማፀን ፍጥረት ሁሉ የሕይወት መሠላል፣ ለኃጢአት መደምሰሻ፣ ለመንግሥተ ሰማይት መውረሻ ድልድይ ሆና የተፈጠረች በልዩ የተመረጠች ፍጥረት ናት።

ሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤል አምላክን በድንግልና እንደምትወልድ በሚያበሥራት ጊዜ ጸጋን የተመላሽ ሆይ ደስ ይበልሽ እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነውና አንቺ ከሴቶች መካከል ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽማለቱም፥ ከተቀደሱ፣ ከከበሩናከተባረኩ ይልቅ አንቺ ቅድስት፣ ንጽሕት፣ ልዩ ነሽ ሲል ነው። <u>ሉቃ 1፥28</u>

<u>ምክንያቱም</u> ከላይ ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው በአዳምና በሔዋን የወደቀው የውርስ ኃጢአትም ሆነ በሌሎች ሴቶች ላይ ያለው መርገምና ሥጋዊ ጠባይዕ (ባሕርይ) ወይም ኅልዮ በእርስዋ ላይ ግን ፈጽሞ የለም።

የመልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ብሥራት ልብ ብለን ካስተዋልነው እመቤታችን ከእናቷ ማኅፀን ጀምራ በእግዚአብሔር የተመረጠች፣ ክብርት፣ ልዩ፣ ንጽሕት፣ ቅድስት፣ ቡርክት መሆኗን ነው እንጂ ወደ ፊት እንደምትሆን አይደለም የሚገልጽልን።

በመሆኑም እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም አምላክን ከመፀነሷ አስቀድማም ከውርስ ኃጢአትና ከነውር ሁሉ ንጽሕት እንደሆነች በተገቢው መንገድ እንረዳለን።

<<አንጺሖ ኪያሃ፣ ቀዲሶ ሥጋሃ ኃደረ ላዕሌሃ>> (አንጺሖ ሥጋሃ ለማርያም ወረሰያ ድሉተ ለተወክፎ ቃለ አብ) ይላል። <u>የማቴዎስ ወንጌል 1፥18</u> <u>ትርጓሜ፥</u> አነጻትም ሲል ነውርና ኃጢአት ኑሮባት ሳይሆን ጠበቃት (ከነውር ሁሉ ከለከላት) ማለት ነው ብሎ አመሥጥሮታል።





አዎ ሰማይን ያለ ምሰሶ ያቆመ፣ ምድርንም ያለ መሠረት ያፀና፣ እነኤርምያስንና እነዳዊትን ገና ሳይወለዱ ከእናታቸው ማኅፀን ሳሉ ለመልካም ሥራ ያዘጋጀ፣ እግዚአብሔር ሁሉን ማድረግ ስለሚችል ለእርሱ አንዳችም የሚሳነው ነገር የለምና እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ከተመረጡት የተመረጠች፣ ከከበሩት የከበረች <u>ልዩ፣ ንጽሕት፣ ቅድስት ቡርክት አድርጎ ፈጥሯታል።</u>
<u>መዝ 135፥6</u> ይህን የሚቃወሙ ካሉ እግዚአብሔርን ሁሉን ማድረግ አይችልም እያሉ እንደሆኑ፣ የእግዚአብሔርን ከሃሊነትንና የባሕርይ አምላክነትን እየተቃወሙ መሆናቸውን በመረዳት ከስሕተታቸው ተመልሰው ንስሓ ሊገቡ ይገባቸዋል።

ምክንያቱም ይህን ያደረገ እግዚአብሔር ስለ ሆነ የእግዚአብሔርን ከሃሊነት፥ ማለትም እግዚአብሔር አምላክ ለእመቤታችንም ሆነ ለሌሎች ቅዱሳን የሰጠውን የማይሻር የአማላጅነት፣ የረድኤት፣ የበረከትና የምሕረት ቃለ ኪዳንን (ቃል ኪዳንን) እንደናቁ፣ የእግዚአብሔርን ዘለዓለማዊ ስጦታ እንዳቃለሉ፣ በእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ አማላጅነት፣ ፍጹም ቅድስና እና ፍጹም ንጽሕና ላይ እንደቀለዱ፥ <u>በአጠቃላይ</u> በማቴዎስ ወንጌል ያለውን፥ በግእዙ ሲጠቀስ፥ <<ሰማይ ወምድር የኀልፍ ወቃልየሰ ኢየኀልፍ>> ሰማይ ከምድር ጋር (ሰማይና ምድር) ያልፋል ቃሌ ግን አያልፍም የሚለውን የማይሻር የእግዚአብሔር ቅዱስ ቃል ወደ ጎን እንደተው ይቆጠራል።

<u>ዘፍጥ, 48፥16, ዘኀል 20፥16, መጽሐ, ጥበብ 4፥16, ማቴ 24፥35 እንመልከት፥ በሚገባ ካስተዋልን በእነዚህ ቅዱሳት ቃላት ውስጥ አማላጅነትንም የሚመለከት ምሥጢር ማግኘት እንችላለን።</u>

አዎ ይህን የሚቃወሙ <u>አንቺ ከሴቶች መካከል</u> ተለይተሽ መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የሌለብሽ፥ በረከተ ሥጋን፣ በረከተ ነፍስን ከልጅሽ ከኢየሱስ ክርስቶስ እያማለድሽ የምታሰጪ ነሽ የሚለውን የቅዱስ ወንጌሉን መሠረት አድርጎ በበቁ አበው ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ሲነገር የሚኖረውን ምሥጢረ መለኮትንና፥ <u>ቅድስት ድንግል ማርያም አምላክን በድንግልና ፀንሳ በድንግልና</u> የወለደች ከአዳም ዘር የተላለፈ ኃጢአት (በዘመናችን ጥንተ አብሶ የሚባለው) ያላገኛት፣ መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የሌለባት ናት ብሎ እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር <u>1988 ዓ.ም</u> <u>(1996) እምነት፣ ሥርዓተ አምልኮና የውጭ ግንኙነት በሚል</u> መጽሐፍ ያረጋገጠውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ ስላልተቀበሉ በእምነታቸው

ከኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን እምነትና ሥርዓተ አምልኮ ውጭ ናቸው ማለት ነው።

<<እምነት፣ ሥርዓተ አምልኮና የውጭ ግንኙነት ምዕራፍ 7፣ ገጽ 4>>

## ክፍል 60፥

## የእመቤታችን ሥርወ ልደት በዐጭሩ ሲገለጽ፥

እመቤታችን በሕጋዊ ሩካቤ ከኢያቄምና ከሐና የተወለደች መሆኗ የታወቀ ነው።

ሥርወ ልደቷም ከቤተ ክህነትና ከቤተ መንግሥት ነው። መዝ 86፥1 ትርጓሜው,ማቴ 1፥1 እንመልከት።

ይኸውም በሀብታቸው እጅግ ታዋቂነት የነበራቸው ቴክታ እና በጥሪቃ የሚባሉ ቅድመ አያቶቿ መክነው (ልጅ አልባ ሆነው) ሲኖሩ ልጅ እንዲሰጣቸው ፈጣሪአቸው እግዚአብሔርን በጸሎት ይማፀኑት ስለ ነበሩ ደግ ልጅን እንደሚወልዱ፥ እንዲያውም ከፍጡራን ሁሉ በላይ የምትሆን ልጅ (እመቤታችን) ከእነእርሱ ዘር መካከል እንደምትወለድ በራዕይ (በሕልም) አማካይነት አስቀድሞ እንደተጠቆመ ከመንፈሳዊ ታሪኩ መረዳት ይቻላል።

የራዕዩ (የሕልሙ) ሁኔታም፥

ነጭ እንቦሳ ከበረታቸው ስትወጣ፥ እንቦሳይቱ ስድስት እንቦሳዎችን ስትወልድ፣ ስድስተኛይቱም ጨረቃን ስትወልድ፣ ጨረቃ ደግሞ ፀሐይን ስትወልድ አዩና ወደ መፈክረ ሕልም (ወደ ሕልም ፈቺ) ሔደው ቢያስፈቱት (ቢያስተረጉሙት) ሕልም ፈቺው ከፍጡራን ሁሉ በላይ የምትሆን ደግ ልጅን እንደሚወልዱ ጠቆማቸው። የፀሐዩ ነገር ግን ስለ አልተገለጸለት አልተረጐመላቸውምና ጊዜ ይተርጉመው በማለት ወደ ቤታቸው ተመለሱ።

ከዚያም በኋላ ሄኤሜንን እንደ ወለዱና በሰባተኛው ትውልድም የእመቤታችን እናት ሐና እንደተወለደች ይታወቃል። የእመቤታችን እናት ሐና አካለ መጠን ስትደርስ ከይሁዳ





ዘር ለተወለደው በደግነቱ እጅግ ለታወቀው ኢያቄም ለሚባለው ደግ ሰው ብትጋባም በእመቤታችን ቅድመ አያቶች የነበረ ምክነት በኢያቄም እና በሐና ላይም ስለቀጠለ ኢያቄምና ሐና መካኖች (ልጅ አልባ) ሆኑ ማለት ነው።

ስለዚህም በዘመኑ በነበረው ሥርዓት መሠረት እግዚአብሔር የተጣላቸው ርጉማን እንደሆኑ ተቈጥረው ከማንኛውም መንፈሳዊ በረከትና ማኅበራዊ ተሳትፎ እንዲገለሉ ይደረግ ነበር።

የዘመኑ አገልጋዮችም (ካህናተ ኦሪትም) እግዚአብሔር የመካኖችን መባ ስለማይፈቅድ (ስለ ማይወድ) እናንተ እግዚአብሔር ልጅን የነሣችሁ መካኖች በመሆናችሁ መባችሁን መቀበል አንችልም እያሉ ያሳዝኑዋቸው እንደ ነበር ይነገራል።

በመሆኑም ኢያቄምና ሐና ልጅን እንዲሰጣቸው እግዚአብሔርን ሁል ጊዜ በኀዘንና በልቅሶም ጭምር ይለምኑት ነበር ማለት ነው። በተለይም ከዕለታት አንድ ቀን ወደ ቤተ እግዚአብሔር (ወደ ጸሎት ቤት) በመሔድ ልጅን እንዲሰጣቸው ፈጣሪኣቸውን አጥብቀው በጸሎት ተማፅነው የሚወልዱት ልጅ ወንድም ይሁን ሴት የእግዚአብሔር አገልጋይ እንጂ የእነእርሱ አገልጋይ እንዲሆን ፈጽመው እንደማይፈልጉ ቃል በመግባት ወደ ቤታቸው ተመለሱና በሐምሌ ወር (እንደ እኛ ኢትዮጵያውያን አቈጣጠር ሐምሌ 30 ቀን) ሐና የኢያቄም ማቆሚያ መልካም ፍሬ አፍርታ ፍጥረት ሁሉ ሲመገባት፥ ለእርሱም ፀምርን ሲያስታጥቁት በሕልም እንዳየች ለኢያቄም ነገረችው።

(ፀምር ማለት ከልዩ ልዩ እንስሳት፥ በተለይም ደግሞ ከበግ ፀጉር የሚሠራ በክብር ጊዜ የሚለበስ ለስላሳና ምቹ የሆነ ልዩ የሐር ልብስ ነው) (ኢዮብ 31፥20, ሕዝ 34፥3, 44፥17, ራዕ ዮሐ 1፥14 እንመልከት)

ኢያቄምም ነጭ ርግብ ሰባቱን ሰማያት ሰንጥቃ መጥታ በሐና ራስ ላይ ስታርፍ በቀኝ ጆሯ ገብታም በማኅፀኗ ስታድር እንዳየ ለሐና ነገራትና ሁለቱም በዚሁ አስደናቂ ምሥጢር ከተወያዩ በኋላ ወደ መፈክረ ሕልም (ወደ ሕልም ፈቺው) ሔደው ጠየቁት። መፈክረ ሕልም (ሕልም ፈቺውም) ደግ ልጅን እንደሚወልዱ ለመግለጽ ሞከረ። እነርሱም ምንም እንኳን ነገሩን በቀጥታ ባይቀበሉትም ፍጻሜው ግን አልቀረም።

በነሐሴ ወር መልአከ እግዚአብሔር ኢያቄምና ሐና ደግ ልጅን (እመቤታችንን) እንደሚወልዱ ነግሮዋቸው እመቤታችን (እንደ እኛ

ኢትዮጵያውያን አቆጣጠር) ነሐሴ 7 ቀን ተፀንሳ ግንቦት 1 ቀን ተወለደች ማለት ነው።

እመቤታችን ገና ሳትወለድ ከእናቷ ከሐና ማኅፀን እያለች ጀምሮ ብዙ ሕሙማን የሐናን አካል (ሰውነት) እየዳሰሱ ከደዌያቸው ይፈወሱ እንደነበር ቅዱስ የሆነ መንፈሳዊ ታሪኩ ይናገራል።

እመቤታችን ሦስት ዓመት ሲሞላት ወላጆቿ ኢያቄምና ሐና በተሳሉት ስዕለት መሠረት ቤተ እግዚአብሔርን እንድታገለግል ከቤታቸው አውጥተው በዘመኑ በነበሩት ካህናት አማካይነት ለቤተ እግዚአብሔር ስለአስረከቧት ሐርንና ወርቅን እያስማማች እየፈተለች፣ እየሠራች፣ ቤተ እግዚአብሔርን እያገለገለች 12 ዓመት በንጽሕና፣ በክብርና በድንግልና ተጠብቃ በቤተ መቅደስ ኖረች።

ከዚህ በኋላም ዮሴፍ በተባለው ደግ የእግዚአብሔር ታማኝ ሰው አማካይነት በክብርና በንጽሕና እንድትጠበቅ ካህናቱና ሕዝብ ስለ ወሰኑ በዚሁ ሁኔታ ላይ እያለች መልአክ እግዚአብሔር ወደ እርሷ መጥቶ (ገብቶ) ደስ ይበልሽ ጌታ ከአንቺ ጋር ነው፤ አንቺ ከሴቶች ሁሉ ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ፥ ማለትም እግዚአብሔር ከሥጋሽ ሥጋን ከነፍስሽም ነፍስን ነሥቶ (ተዋሕዶ) አንድ አካል አንድ ባሕርይ ይሆናልና (ከአንቺ ይወለዳልና) በነቢያት ትንቢት በመላእክት ተልእኮ ደስ ያለሽ ምልዕተ ክብር ሆይ፤ <u><<ተፈሥሒ>></u> ደስ ይበልሽ ብሎ ባበሠራት መሠረት የፍጥረት ሁሉ መድኃኒት፥ ለኃጥኣን ተስፋችንና ሕይወታችን የሆነውን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በድንግልና ጸንሳ በድንግልና ወለደችልን።

ለሰው ልጆች ሁላችን የይቅርታ ፀወንና የምሕረት መሰላል፣ የመንግሥተ ሰማያት ድልድይ ሆነች ማለት ነው።

ከዚህም በኋላ በስደት መከራና በልዩ ልዩ ኀዘን ቆይታ <u>በ64 ዓመት ዕድሜዋ ጥር 21 ቀን ዓርፋ</u> ወደ ገነት ተወሰደች። በአባቶች ሐዋርያት ጸሎትና ልመና ተመልሳ መጥታም <u>ነሐሴ 15 ቀን</u> ሐዋርያት ቀብሯት ነሐሴ 16 ቀን ከመቃብር ተነሥታ በክብርና በልዩ ልዩ ምስጋና ወደ ሰማይ ዐረገች።

<u>ስድሳ አራት ዕድሜዋ ሲተነተንም፥</u> <u>በናት በአባቷ 3 ዓመት፤</u> በቤተ መቅደስ <u>12 ዓመት፤</u> በቤተ ዮሴፍ 9 ወር፣ ከልጅዋ ጋር በስደትና በልዩ ልዩ ቦታ <u>33 ዓመት ከ 3 ወር፤</u> በቤተ ዮሐንስ (ከዮሐንስ ጋር) 15 ዓመት ጠቅላላ ዕድሜዋ <u>ሲደመር 64 ዓመት ይሆናል ማለት ነው።</u>





## ክፍል 61፥

## ከዚህ ቀጥሎም ስለ ዕረፍቷ፣ ስለ ትንሣኤዋና ስለ ዕርገቷ፥ መሠረታዊ ዝርዝር በየደረጃው ባጭር ባጭሩ ይብራራል።

## የእመቤታችን ዕረፍት፥

ሁል ጊዜ በቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን የጉባኤ መድረክ እንደሚገለጸው እመቤታችን ጥር 21 ቀን ዓርፋ ሐዋርያት ሊቀብሯት ይዟት እየሔዱ እያሉ አይሁድ ከሐዋርያት እጅ ነጥቀው በእሳት ለማቃጠል በመወሰን ስለ ደረሱባቸው ሐዋርያት የአይሁድን ኃይለኛ ግስጋሴ በተመለከቱ ጊዜ ደንግጠው ትተዋት ሸሽተው ነበርና በእግዚአብሔር የታዘዘ መልአክ እግዚአብሔር በጌታው አደራ የተባለው ዮሐንስም ከእርሷ ጋር ስለ ነበር ሁለቱን በደመና ነጥቆ በመውሰድ እመቤታችንን በገነት ከዕፀ ሕይወት ሥር እንዳኖራት ቅዱስ ታሪኩ ይገልጻል። <u>ዮሐ 19፥26</u>

## ክፍል 62፥

## ቀብሯ፣ ትንሣኤዋ፣ ፍልሰቷና ዕርገቷ፥ (ፍልሰታ ለማርያም)።

ሐዋርያት አይሁድ በደረሱባቸው ሰዓት ፈርተው ትተዋት በመሔዳቸው አዝነው ከነሐሴ 1 ቀን ጀምረው ለሁለት ሰባት (ለ14 ቀናት ያህል) ሱባኤን በመያዝ ፈጣሪኣቸው እግዚአብሔርን ስለ ለመኑ <u>በ15ኛው ቀን</u> እመቤታችንን አግኝተዋት በክብርና በምስጋና ስለቀበሯት በ3ኛው ቀን ከመቃብር ተነሥታ በልዩ ልዩ ምስጋና ወደ ሰማይ ዐረገች።

ከሞት ወደ ዘለዓለማዊ ሕይወት ፈለሰች፣ ተሰደደች ማለት ነው።

ይኸውም እመቤታችን ወደ ሰማይ በምታርግበት ጊዜ በቀብሯ ስነ ሥርዓት ያልተገኘ ቶማስ ሐዋርያ የበቃ ነውና ከሀገረ ስብከቱ በደመና ወደ ሐዋርያት ሲመጣ ከሰማይ ስለ ተገናኙ ደነገጠ። በቀብሯ ስነ ሥርዓት ባለመገኘቱም እጅግ አዘነ።

እመቤታችን ግን እነርሱ ያላዩትን ትንሣኤዋንና ዕርገቷን አንተ ብቻ አይተኸልና አይዞኽ አትዘን ብላ አረጋግታ፥ ማረጓን ለሐዋርያት እንዲነግራቸው፣ ለምልክትና ለበረከት እንዲሆናቸውም ተገንዛበት ከነበረው ሰበን ሰጥታ ሰደደችው።

ቶማስም ወደ ሐዋርያት በመሔድ ያላወቀና ያላየ መስሎ ስለ እመቤታችን ጉዳይ ሐዋርያትን ጠየቃቸውና እኛስ አግኝተን ቀበርናት አንተ ግን ለዚህ አልታደልኽም አሉት።

እርሱም ይህማ እንዴት ይሆናል ያረፈችው በጥር ወር አሁን ቀበርናት የምትሉት በነሐሴ ወር ማንስ በዚሁ ያምናል በማለት ለመከራከር ስለ ሞከረ አንተ ሁል ጊዜ ተጠራጣሪ ነኽ ድሮም ጌታችንን <<የተወጋኸውን ጎንህን ሳላይ አላምንም>> ብልኸው ነበር አሁንስ ለራስህ ተጠራጥረኽ (መናፍቅ ሆነህ) ሌላውንም ስታጠራጥር (ግራ ስታጋባ) ልትኖር ፈልገህ ነውን? በማለት መቃብሩን ከፍተው ሊያሳዩት ቢሞክሩ እመቤታችንን ከመቃብር ውስጥ አጡዋትና ደነገጡ።

ምናልባትም አይሁድ በሌሊት ሰርቀው ወስደዋት ይሆኑ ይሆኑደ? ብለው በመገመት ሊሆን ይችላል፥ አዘኑ ማለት ነው።

<<ስለ ቶማስ የጌታችንን ጎን መዳሰስ ወንጌለ ዮሐንስ 20፥24>>

ሐዋርያ ቶማስም በሉ አይዛችሁ አትደንግጡ እመቤታችንስ ዐርጋለች እኔ አግኝቻታለሁ ብሉ ምሥጢሩን ሁሉ እንደ ነገራቸው፤ ለምልክትና ለበረከት ይሆናቸው ዘንድ እንዲካፈሉት እመቤታችን የሰጠችውንም ሰበን እንደሰጣቸውና ሁሉም እንደ ተካፈሉት ታሪኩ ይናገራል።

(ሰበን እመቤታችን ተገንዛበት የነበረ ልዩ ልብስ ማለት ነው)

ከዚህ በኋላ ሐዋርያት ቶምስ ትንሣኤሽንና ዕርገትሽን አይቶ እኛ ግን ሳናይ ብለው ልክ እንደበፊቱ በነሐሴ 1 ቀን ሱባኤ ይዘው ጌታችንን በጸሎት ስለ ጠየቁ ነሐሴ 16 ቀን እመቤታችን መጥታ በግልጽ አይተዋት፥ ጌታችን እመቤታችንን እንደ መንበር፣ ቅዱስ ጴጥሮስ ሐዋርያን ተራዳዒ ካህን፣ ቅዱስ እስጢፋኖስ ሰማዕትንም ሠራዒ ዲያቆን አድርጎ ራሱ ቀድሶ እንዳቈረባቸው ቅዱስ የሆነ መንፈሳዊ ታርኩ ያስረዳል።

<<ምንጩን ከውዳሴ ማርያምና ቅዳሴ ማርያም ትርጉም በስተመጨረሻው እንመልከት>>





## ክፍል 63፥

## ስለ ፍልሰትና ፍልሰታ ለማርያም መሠረታዊ ዝርዝር፥

በልሳነ ግእዝ (በግእዝ ቋንቋ) <<ፈለሰ>> ብሎ ተሰደደ ይላልና ፍልሰት ለሚለው ዘር ስደት የሚል ትርጉም ነው ሊኖረው የሚችል።

ትንታኔውና ምሥጢራዊ ትርጉሙ ደግሞ ከአንድ ሥፍራ ወደ ሌላ ቦታ መሰደድ ወይም ከሥር ጨርሶ መነቀል፣ መፍለስ፥ ማለት ነው።

ለወንድ ፈላሲ፣ ለሴት ደግሞ ፈላሲት ይባላል።
ትርጉሙ፥ ስደተኛ ማለት ነው።

የትርጉሙ ትንታኔም ፈላሲ ወይም ፈላሲት ማለት፥
ከአንዱ ሥፍራ ወደ ሌላው ሥፍራ በተለያየ ምክንያት የተሰደደ (የተሰደደች) ስደተኛ ማለት ሲሆን፥ ምሥጢሩ ሲራቀቅ ደግሞ ፍልሰት ማለት ከዚሁ ከጊዜያዊው የዓለም ደስታ መሰደድ ማለት ነው።

ፈላሲ ስደተኛ፣ የተሰደደ፥ ከቂም፣ ከበቀልና ከክፋት ሁሉ የራቀ፥ ጥሩ ጥሩን ከመብላት፣ ከመጠጣት መጾምን የመረጠ፣ ከኃጢአት ሥፍራ ወደ ጽድቅ ቦታ የተሰደደ፥ ከሞት ወደ ዘለዓለማዊ ሕይወት የተሸጋገረ፥ ከምድር ወደ ሰማይ ያረገ (የወጣ) ኃጢአትን ከመሥራት ይልቅ ጽድቅን መሥራት የወደደ፤

በአጠቃላይ ገንዘቡንና ንብረቱን ሁሉ ለእግዚአብሔር እንግዶች ለነዳያን መጽውቶ፣ ወይም ለቤተ እግዚአብሔር ሰጥቶ ከዚሁ ከኃላፊው፣ ከጠፊው የዓለም ተድላ ደስታ፥ ከምቾቱም ሁሉ ወደ መከራ የመነነ፥ የሚያስደስተውንና የሚያስጐመጀውን ሁሉ ለመንግሥተ ሰማያት ሲል ፈጽሞ የተወ የክርስቶስን መከራ መስቀል የተሸከመ ማለት ሊሆን ይችላል።

ይኸውም መጽሐፋዊ ምሥጢሩና መንፈሳዊ መልእክቱ ሁላችንንም ስለሚመለከት ብናደርገው መልካም ነው።

ይህን ብናደርግ የማያልፈውን ዘለዓለማዊውን ሕይወት ማግኘት እንችላለን ማለት ነው።

## ክፍል 64፥

## ማጠቃለያ፥

የእመቤታችን ፍልሰተ ሥጋ (ፍልሰቷ) ስንልም ከዚህ በላይ ከመሠረቱ ጀምረን እንደተመለከትነው ከሞት ወደ ሕይወት የፈለሰችበት ከመቃብር ተነሥታ ወደ ሰማይ የወጣችበት፣ (ያረገችበት) ማለታችን ሲሆን፥ እኛ ሕዝበ ክርስቲያን ከእርሷ በረከት ለመሳተፍ፣ በእርሷ አማላጅነት ዘለዓለማዊ ሕይወትን ለማግኘት ስንል በየዓመቱ ከነሐሴ 1 ቀን ጀምሮ እስከ ነሐሴ 15 ቀን ድረስ የሚገኘውን ወቅት፥ ፈጣሪያችንን በማመስገን ለቃል ኪዳን እናታችን፣ ለአማላጃችን ለቅድስት ድንግል ማርያም ልዩ ልዩ ዝማሬን በማቅረብ ሱባኤ ይዘን ለየት ባለ መልኩ እንጾመዋለን። ኃጢአታችንን ይቅር እንዲለን ፈጣሪያችንን እንለምንበታለን። ሃይማኖታዊ ሥርዓታችንንና ክርስትያናዊ ግዴታችንንም እንፈጽምበታለን።

አዎ በአጠቃላይ ፍልሰትና በየዓመቱ ከነሐሴ 1 ቀን ጀምሮ ለ15 ቀናት ያህል እውነተኛው ክርስቲያን፣ የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ ወዳጅ የቃል ኪዳኗ ልጅ የሆነ ሁሉ በጸሎትና በልዩ ሱባኤ የሚጾመው ፍልሰታ (ፍልሰቷ) በመባል የሚታወቀው ትርጉሙና መሠረታዊ ምሥጢሩ በዐጭሩ ሲገለጽ ይህን ይመስላል።

የፍልሰታ ለማርያም ወቅትና ሳምንት ሁሉም እውነተኛው ሕዝበ ክርስቲያን የሚጾመው፥ ከእመቤታችን ጋር ያለውን የቃለ ኪዳን ትስስር በጾም፣ በጸሎትና በልዩ ልዩ ዝማሬ የሚገልጽበት ከሌላው ጊዜ የተለየ የሱባኤና የምስጋና ሳምንት ነው።

ይኸውም ለክርስቲያናዊ እምነታችንና ለሰማያዊ ተስፋችን እውነተኛ መታወቂያ ሲሆን፥ እኛ በእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ አማላጅነት፣ በእግዚአብሐር የባሕርይ አምላክነትና መሓሪነት የምናምን፥ በመላእክት ተራዳኢነት፣ በጻድቃንና በሰማዕታት በረከት ረድኤት፥እንዲሁም አማላጅነት የምንማፀን የእግዚአብሔር ቤተሰቦች መሆናችንን በተግባር የምናረጋግጥበት ወቅት ነው።

የእግዚአብሔር ቸርነት፣ የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ አማላጅነት፣ የመላእክት ተራዳኢነት፣ የቅዱሳን፣ የጻድቃንና የሰማዕታት በረከት፣ ረድኤት፣ እንዲሁም አማላጅነት ሁል ጊዜ አይለየን።



<< እመቤታችን ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ >>

በተጨማሪም ከዚህ ቀጥለው ያሉትን ጥቅሶች እንመልከታቸው፥

ግእዝ 1ኛ <<ኵለንታኪ ሠናይት እንተ ኀቤየ አልብኪ ነውር ወኢምንትኒ ላዕሌኪ>>

ትርጉሙ፥ ወዳጄ ሆይ ሁለንተናሽ ውብ ነው፥ ነውርም የለብሽም ይላል። መሐልየ (መኃልየ) ሰሎሞን 3 (4)፥7

ይህ እመቤታችን ምንም ነውር እንደሌለባት አስቀድሞ የተነገረ ነው።

2ኛ <<ናሁ እምይእዜሰ ያስተበፅዑኒ ኵሉ ትውልድ>> እነሆም ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል። (ከእንግዲህስ ወዲህ ትውልድ ሁሉ ያመሰግኑኛል ይላል በትርጓሜው) ይህ ቅዱስ ቃል እመቤታችን ከእግዚአብሔር በታች በፍጥረት ሁሉ ስትመሰገን የምትኖር መሆኗን ነው የሚያረጋግጥልን። ሉቃ 1፥48

3ኛ ስለ አማላጅነቷም፥ ኢየሱስ እናቱን (ድንግል ማርያምን) ይወደው የነበረው ደቀ መዝሙሩን (ዮሐንስን) ባጠገቡ ቆሞ ባየ ጊዜ አንቺ ሴት እንሆ ልጅሽ አላት፣ ከዚህ በኋላም ደቀ መዝሙሩን እናትህ እነኋት አለው። ዮሐ 19፥26

እኛ ሕዝበ ክርስቲያንም በቃል ኪዳኗ ስለምንማፀን የእመቤታችን የአደራ ልጆች ነን ማለት ነው።

4ኛ <<ነቢይ (ጻድቅ) ነውና ስለ አንተም ይጸልያል፤ ትድናለህም>> ይህን በልብህ ቅንነት እንዳደረግህ እኔ አወቅሁ፤ እኔ ደግሞ በፊቴ ኃጢአትን እንዳትሠራ ከለከልሁህ። ዘፍ 20፥6,7

<<ቅዱስ ቃሉ ስለ አማላጅነትና በእግዚአብሔር ሕግ ከገቢረ>> ኃጢአት (ኃጢአትን ከማድረግ) ስለ መታቀብ ያስረዳል።

5ኛ ከክፉ ነገር ያዳነኝ መልአክ እርሱ እነዚህን ብላቴኖች ይባርክ። ዘፍ 48፥16,መዝ 33፥7።

6ኛ <<ኤልያስ እርሱ ባለበት ቤት የሞተውን ብላቴና በእግዚአብሔር ኃይል አሥነሣው>> 1ኛ ነገ 17፥22

7ኛ <<ኤልሳዕም ወደ እግዚአብሔር ጸልዮ የሞተውን ሕፃን

## << ስለ ባሕረ ሓሳብ ዐጭር መግለጫ >>

(ከክርስቶስ ልደት በፊት የነበረው 5500 ዘመን ሁሉ የፍዳ፣ የኩነኔ፣ የጨለማና የችግር ዘመን ነው ማለት ነው)

(አሠርቱ ምዕት ወተሥዓቱ ምዕት ተሥዓ ወተሥዓቱ ኮነ ዓመተ ሥጋዌ ወዓመተ ምሕረት)

ከክርስቶስ ልደት ወዲህ ያለው 1998 ዘመን ግን ጌታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ በመስቀል ተሰቅሎ ስለ አዳነን የሥጋዌ ወይም የሰው መሆን፣የምሕረትና የይቅርታ ዘመን ይባላል ማለት ነው።

ዮም ሠረቀ ለነ ወርኀ ቡሩክ ሰኔ በዕለተ ሓሙስ ያብፅሐነ እግዚአብሔር እስከ ወርኀ ቡሩክ ሓምሌ ዘይሠርቅ በዕለተ ቀዳሚት በሰላም ወበዳኅና፤ ኃምሱ ሠርቀ መዓልት፣ አሥሩ ወአሚሩ ሠርቀ ሌሊት፤ ሰዱሱ ሠርቀ (ጥንተ ፀሐይ ወወርኅ) ሰኑዩ ጥንተ ዕለት።

<u>የዚህ ዐጭር ትርጉም፥</u> የጌታችንን አዝማናትንና ጊዜያትን ከዘመነቅዱስ ማርቆስ ወንጌላዊ ሆነን ስናስታውሰው ወደ ቅዱስ ሉቃስ ዘመን እንዲያደርሰን እየጸለይን ነው።

ዛሬ ቀኑ እንዳለ 5 ሲባል ሌሊቱ ደግሞ ከላይ ከፍ ብሎ እንደተገለጸው ከአበቅቴ፣ ከዕለቱና ከሕፀፅ ጋር ተደምሮ 11 ይሆናል ማለት ነው።

ሁሉንም ማድረግ የሚቻለው ፈጣሪያችን ልዑል እግዚአብሔር ልባዊ ትሕትናን፣ እውነተኛ ፍቅርን፣ ሰላሙንና አንድነቱን ይስጠን

አሜን።

<u>1998</u> (2006)

**Po.box 41435**
**Arlington, VA, 22204።**

**<u>U.S</u>**